ሰኔ 20/ 2015 ዓ.ም

ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች

የ2014 በጀት ዓመት የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት እና

የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

የተጠቃለለ አጭር ሪፖርት

የተከበሩ አፈ ጉባዔ!

የተከበሩ ም/አፈ ጉባዔና

የተከበሩ የመንግስት ወጪ አስተዳደር ቁ/ጉ/ቋ/ኮ/ሰብሳቢ

የተከበራችሁ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት!

ክቡራትና ክቡራን!

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በኢ.ፌዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 101 ንዑስ አንቀፅ 2 እና መሥሪያ ቤቱን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 አንቀጽ 5 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 15፤ እንዲሁም በአንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 4 እና በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 1146/2011 አንቀጽ 2 መሰረት ለፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተሰጠው ስልጣን መ/ቤቱ ኦዲት ያደረገውንና ያስደረጋቸውን የመንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች የኦዲት ሪፖርት፣ የፌዴራሉ መንግሥት ለክልሎች ለአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ፣ ለመልሶ ማቋቋምና ለልማት ማስፋፊያ ለሚያስፈልጋቸው ወጪ የሚያደርገውን ድጎማ በአራት ክልሎች የተከናወነውን ኦዲት ሪፖርት፣ በኢንቨስትመንት ፋይናንሲንግ የፍትሃዊነት መሠረታዊ አገልግሎት ለሁሉ ዓቀፍ የዕድገት ተጠቃሚነት ፕሮግራም (Enhancing Shared Prosperity through Equitable Service-ESPES) የተከታታይ እና የማረጋገጫ ኦዲት የተከናወኑ ኦዲት ሪፖርቶች፣ የመንግሥት መ/ቤቶች አሠራር ህጉን የተከተለ፣ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አሠራር የተፈጸመ፣ ተፈላጊውን ግብ የመታና ውጤት ያስገኘ መሆኑን ለማረጋገጥ የተደረገውን የክዋኔና አካባቢ ኦዲት፣

እንዲሁም ስለመ/ቤቱ አጠቃላይ ሥራዎች ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ዓመታዊ ሪፖርት እንደሚያቀርብ በተደነገገው መሠረት የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲትና በተመረጡ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ላይ የተከናወኑ የክዋኔ ኦዲቶች ዕቅድ ክንውንና የኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

በዚህ ሪፖርት ውስጥ የተካተቱት፤

1. በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሂሳብ ላይ የተከናወኑ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት፣ የፌዴራሉ መንግሥት ለክልሎች ለአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ፣ ለመልሶ ማቋቋምና ለልማት ማስፋፊያ ለሚያስፈልጋቸው ወጪ የሚያደርገውን ድጎማ በአራት ክልሎች የተከናወነውን ኦዲት ሪፖርት፣ የክዋኔ ኦዲት እና የፍትሃዊነት መሠረታዊ አገልግሎት ለሁሉ ዓቀፍ የዕድገት ተጠቃሚነት ፕሮግራም (Enhancing Shared Prosperity through Equitable Service-ESPES) የተከታታይ እና የማረጋገጫ ኦዲት፣ የማጠቃለያ ሂሳብ ኦዲት እና የፌዴራል መንግስት አጠቃላይ የገቢና ወጪ ሂሳብ በተመለከተ የተከናወኑ ኦዲት ሪፖርቶች ናቸው፡፡
2. ሪፖርቱ በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና የሙያ ፈቃድ በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶች ኦዲት የተደረጉትን የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ሂሳብና በመንግስትና የልማት አጋር ድርጅቶች እርዳታና ብድር የሚካሄዱ ፕሮጀክቶች/ፕሮግራሞችን ኦዲት ያካትታል፡፡
3. የ2014/15 ኦዲት ዓመት የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች ሂሣብ የኦዲት ዕቅድ ክንውን እና ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች፣ የመሥሪያ ቤቱን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ፣ በኦዲት ሥራ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች እና የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን አጭር የሥራ እንቅስቃሴን ያጠቃለለ ነው፡፡
4. የ2014 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲትን በተመለከተ በመ/ቤታችን የተከናወኑ ዝርዝር የኦዲት ሪፖርቶች ራሳቸውን ችለው በተጠናቀሩ 2 ጥራዞች የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያልተቻለባቸው 6 መ/ቤቶችና የጎላ ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠባቸው 19 መ/ቤቶች እንዲሁም 23 አዳዲስ፣ 8 ክትትልና 1 ካለፈው ዓመት የዞረ በድምሩ 32 የክዋኔ ኦዲቶችን ለም/ቤቱ የቀረቡ ስለሆነ እነዚህን ሪፖርቶች የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎችም የሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎች በሚገባ በመመርመር አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ እንዲያስችል በጥልቀት ተዘጋጅቷል፡፡

በተጨማሪም የእነዚህ ሪፖርቶች ቅጅ 2 ጥራዞች እና ሌሎች የተጠቀሱት ሪፖርቶች በሶፍት ኮፒ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤትም እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

5. እያንዳንዱ የኦዲት ሥራ እንደተጠናቀቀ ከሚመለከታቸው የኦዲት ተደራጊ መ/ቤት ኃላፊዎች ጋር በኦዲቱ ግኝቶች ላይ የመውጫ ስብሰባ (Exit Conference) ከመደረጉም በተጨማሪ ረቂቅ የሥራ አመራር ሪፖርት ተልኮላቸው መ/ቤቶቹ ለሥራ አመራር ሪፖርቱ የሰጡትን ምላሽ ያገናዘበ በመሆኑ የመረጃዎቹ ተአማኒነትና አግባብነት በሁሉም ወገን ተቀባይነት እንዳለው ይታመናል፡፡

6. ኦዲቱ የተከናወነው በዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎች ሲሆን፤ ለኦዲቱ መሰረት የሆኑት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት፣ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ያቀረቧቸው የሂሣብ መዛግብት፣ ሰነዶች፣ የሂሣብ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች ሲሆኑ ኦዲቱም የተከናወነው በአብዛኛው የተለመደውን የአልፎ አልፎ ወይም የናሙና ኦዲት ስልት በመከተል፣ እንዲሁም እንደ ኦዲቱ አስፈላጊነትና አግባብነት ሙሉ በሙሉ ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

ያለፈው አመት ኦዲት በተሰጠው አስተያየት መሰረት የተወሰዱ እርምጃዎች

7. በ2013 በጀት ዓመት እና ከዚያ በፊት በተከናወኑ የኦዲት ሪፖርቶች መሠረት እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ86 መ/ቤቶች ተመላሽ እንዲደረግ ተብሎ አስተያየት ከተሰጠበት ብር 6,883,555,669.74 ውስጥ ተመላሽ የተደረገ ብር 44,995,283.14 መሆኑ ታውቋል፡፡ ይህ አፈጻጸም ተመላሽ ሊደረግ ከሚገባው ሂሳብ ጋር ሲነፃፀር በመቶኛ 0.65 % ብቻ ሲሆን፤ ቀሪው ብር 6,838,559,886.60 ተገቢው እርምጃ ያልተወሰደበትና ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ ምንም እንኳ የተመለሰው ገንዘብ አጥጋቢ ባይሆንም በተሰጠው አስተያየት መሰረት ጥረት በማድረግ አብዛኛውን ተመላሽ ያደረጉ ተቋማት፤ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት ከተሰጠበት ብር 9,795,232.36 ውስጥ ብር 9,750,571.48 (99.54 %)፣ የፌዴራል ቴክኒክ ትምህርትና ሥልጠና ኢንስቲትዩት ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት ከተሰጠበት ብር 14,896,989.09 ውስጥ ብር 14,760,365.46 (99.08%) እና የቅዱስ ጴጥሮስ እስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት ከተሰጠበት ብር 6,386,572.86 ውስጥ 5,095,250.31(79.78%) ተመላሽ አድርገዋል፡፡

8. የመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ መልኩ በ 2013/2014 በጀት አመት የተሰሩትን 9 የፋይናንሻልና ህጋዊነት ኦዲትን እና 19 የክዋኔ ኦዲትን ተለይቶ በቀረበለት መሰረት ይፋዊ የህዝብ ስብሰባዎች እና 8 መስክ ምልከታዎች አካሂዷል፡፡ በዚሁ መሰረትም ይፋዊ ዉይይቱ በሚደረግበት ወቅትም የኦዲት ግኝቱን ባህሪ መነሻ በማድረግ አቅጣጫዎች የተቀመጡ ሲሆን የባለድርሻ አካላትም የተቋማቸውን ተግባር እና ሃላፊነታቸዉን መነሻ በማድረግ የሚከተሉትን እርምጃዎች ወስደዋል፡፡

ፍትህ ሚኒስቴር በ2013 በጀት አመት ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት በተሰጣቸዉ 39 መ/ቤቶች ላይ እና የኦዲት አስተያየት መስጠት ባልተቻለባቸዉ 8 መ/ቤቶች በድምሩ ለ47 መ/ቤቶች በኦዲት ግኝት ላይ የወሰዱትን የእርምት እርምጃ እንዲያሳውቁ በደብዳቤ የጠየቀ መሆኑ፣ የገንዘብ ሚኒስቴር በ14 መ/ቤቶች ላይ የገንዘብ ቅጣት እና ከባድ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያና አስተዳደራዊ እርምጃ የወሰደ መሆኑ፡፡

9. ምንም እንኳን ኦዲቱ በናሙና በመሆኑ ሙሉ በሙሉ ማረጋገጫ መስጠት ባይቻልም በዚሁ አግባብ በተሰራዉ ኦዲት ለሶስት ተከታታይ አመት ከ2012 እስከ 2014 በጀት አመት አጥጋቢ ውጤት ያገኙ፡- የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት፣ የከተማ መሰረተ ልማት ሚ/ር፣ የኢትዮጵያ ህበረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት፣ የኢትዮጵያ ጤና መድህን አገልግሎት፣ አማኑኤል የአዕምሮ እስፔሻላይዝድ ሆስፒታል እና የኢትዮጵያ የደምና ቲሹ ባንክ አገልግሎት ሲሆኑ ሊመሰገኑ እና በዚሁ አግባብ እንዲቀጥሉ ለማሳሰብ እወዳለሁ፡፡

የ2014 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች

ኦዲት ዕቅድና ክንውን

የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲትን በተመለከተ

10. በመ/ቤቱ አደረጃጀት መሠረት የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችን ኦዲት የሚያደርጉ ስድስት ኦዲት ዳይሬክቶሬቶች፣ የክልሎች ድጋፍና ድጎማ ሂሳብ ኦዲት የሚያደርግ አንድ ዳይሬክቶሬት እና በ1 የልዩ ኦዲት ዳይሬክቶሬት በአጠቃላይ በ8 ዳይሬክቶሬት የተዋቀረ ሲሆን፤ ከየካቲት /2014 እስከ ጥር 30/2015 ድረስ በ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ አቅራቢ ከነበሩት 180 የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች መካከል 165 መ/ቤቶችንና 55 ቅርንጫፎች የድጋፍና ድጎማ 265 ተከታታይ፣ 50 ማረጋገጫ እና

1 ማጠቃለያ በድምሩ 316 እንዲሁም የመንግስት አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሳብ ኦዲት በመ/ቤታችን፤ የተቀሩትን 15ቱን ደግሞ በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት በማስደረግ የኦዲት ሽፋኑን 100% ለማስቀጠል ታቅዶ ነበር ፡፡

11.የፋይናንስና ህጋዊነት እቅድ አፈጻጸም የ164 መ/ቤቶችና 52 ቅርንጫፎች ኦዲት ተጠናቆ ሪፖርቱ ወጪ የተደረገ በመሆኑ አፈጻጸሙ 99.4% ሆኗል፡፡ በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ በአዲስ የተዋሃዱ እና በፈረሱ መ/ቤቶች ምክንያት በዕቅድ ከተያዘው በተጨማሪ 23 መ/ቤቶች ከ 3 ወር እስከ 7 ወር ያለው የሒሳብ ኦዲት ሥራ ተከናውኗል፡፡

<u>የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት በተከናወነባቸው መ/ቤቶች</u>

<u>የሂሳብ መግለጫ ላይ የተሰጡ የኦዲት አስተያየቶች</u>

12.የ2014 በጀት ዓመት የኦዲት አስተያየት ከ2012 እና 2013 በጀት ሂሳብ ኦዲት ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር በማነፃፀር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

መግለጫ /የተሰጠው የኦዲት አስተያየት/	ኦዲት የተደረጉ ሂሳቦች ብዛት		
	2012	2013	2014
ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት	10	51	73
ከጥቂት ጉድለቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ሆነው የተገኙ	46	73	66
አስተያየት ለመስጠት ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች	8	8	6
የጎላ ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠባቸው	41	39	19
በፀጥታ ምክንያት ኦዲቱ ያልተሰራ	1	4	1
የመውጫ ስብሳባ ያልተካሄደባቸውና ለስራ አመራር ሪፖርት ምላሽ ያልሰጡ በመሆኑ በዚህ ሪፖርት ያልተካተቱ	12	2	
ሂሳባቸውን በወቅቱ ስላልዘጉ ኦዲት ያልተደረጉ		1	
ቢሮ ባለመስጠት ኦዲት ያልተደረጉ		1	
ድምር	**118**	**179**	**165**

<u>በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የፋይናንስና</u>

<u>ሕጋዊነት ኦዲት ወቅት የታዩ ዋና ዋና ግኝቶች</u>

13. መ/ቤታችን ምክር ቤቱ ለ2014 በጀት ዓመት ያጸደቀው በጀት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ በሚፈቅድው መሠረት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ ባከናወነው ኦዲት የሂሳብ አያያዝ ግድፈቶች እና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች፣ እንዲሁም አፈጻጸማቸው ከህግና አሠራር ውጭ የሆኑ ሁኔታዎች የተገኙ ሲሆን በዚህ ሪፖርት ትኩረት የሚሹ ዋና ዋና ግኝቶች ብቻ ተጠቃለው እንደሚከተለው ቀርበዋል::

<u>የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ ኦዲት</u>

<u>የጥሬ ገንዘብ ጉድለት</u>

14. በጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ላይ ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 172,466.12 እና በሞያሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ብር 1,134,396.95 በድምሩ ብር 1,306,863.07 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት መኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

15. የጥሬ ገንዘብ ጉድለት በአስቸኳይ ተመላሽ እንዲደረግ፤ እንዲሁም የተሰጣቸውን ኃላፊነት ዘንግተው ገንዘቡን ባጎደሉ ሰራተኞች ላይ አስዳደራዊም ይሁን ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ እና በጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያው መሰረት ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

16. በተጨማሪም የኢ.ፌዴሪ ገንዘብ ሚኒስቴር ባስተላለፈው መመሪያ መሰረት ከብር 50,000.00 በላይ የሚፈጸሙ ክፍያዎች በባለመብቱ ሥም በቼክ ወይም በትራንስፈር መፈጸም ሲገባው በሶስት ዩኒቨርሲቲዎች፣ በአንድ ኮሌጅ በድምሩ ብር 7,964,444.04 እና በግብርና ሚኒስቴር የሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ ብር 255,645.48 በጠቅላላው ብር 8,220,089.52 በባለመብቱ ሥም በቼክ መክፈል ሲገባቸው ክፍያውን በጥሬ ገንዘብ የፈጸሙ መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል።

17. በመመሪያ ከተፈቀደው በላይ በጥሬ ገንዘብ ክፍያ መፈጸም የመንግሥት ገንዘብ ላልተገባ ዓላማ እንዲውል ምክንያት ሊሆን ስለሚችል ተቋማቱ መንግሥት የዘረጋውን የክፍያ ሥርዓት እንዲተገብሩ እንዲሁም የገንዘብ ዝውውሩን ለመቆጣጠር መንግሥት ያወጣው መመሪያ ተግባራዊ እንዲሆን ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ እንዳለባቸው አሳስበናል።

ውዝፍ የተሰብሳቢ ሂሳብ

18.በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት ቀናት ውስጥ እንዲሁም በመመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ደግሞ ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዝዛል፡፡ ይሁን እንጂ ኦዲት በተደረጉ በ131 መ/ቤቶች በጠቅላላው ብር 15,125,179,526.64 በደንቡ መሠረት በወቅቱ ያልተወራረደ (ያልተሰበሰበ) ሂሳብ መኖሩ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

19. በወቅቱ ያልተወራረደ ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ ከተገኘባቸው መ/ቤቶች፡- የጤና ሚኒስቴር ብር 4,517,373,748.55፣ የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ብር 2,835,401,433.21፣ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ብር 1,015,705,316.48፣ የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ብር 1,006,039,843.55፣ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን፣ 797, 023,597.75 እና የትምህርት ሚኒስቴር ብር 747,496,001.47 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

20. በወቅቱ ያልተወራረደ ውዝፍ ተሰብሳቢ ሒሳብ ዕድሜ በቆይታ ጊዜው ሲተነተን፤ ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ብር 5,580,716,484.58 ፣ ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት ብር 4,422,295,130.63፣ ከአምስት ዓመት እስከ አሥር ዓመት ብር 4,597,483,529.42፣ ከአሥር ዓመት በላይ ብር 66,086,713.32 ሲሆን፤ ቀሪው ሂሳብ ብር 458,597,668.69 የቆይታ ጊዜው በግልጽ ለመለየት ያልተቻለ ነው፡፡

21. ከላይ ከተጠቀሰው በተጨማሪም ተሰብሳቢ ሂሳብ የሂሳብ ሌጀር ተከፍቶለት ተገቢው ክትትል እየተደረገበት በወቅቱ የሚሰበሰብ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በ10 መ/ቤቶች ብር 464,454,631.00 ማስረጃ ባለመቅረቡ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልቻለ ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ ታውቋል፡፡

22. በመሆኑም ተሰብሳቢ ሂሳቦቹ ከዓመት ወደ ዓመት ሳይወራረዱ በሂሳብ መግለጫዎቹ ላይ የሚታዩ ከሆነ የሂሳብ መግለጫዎቹን ተዓማኒነት ሊያሳጡ ከመቻላቸውም በላይ የመንግሥት ገንዘብ ለብክነትና ለጥፋት ሊዳረግ የሚችል ስለሆነ መሥሪያ ቤቶቹ በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት የቅድሚያ ክፍያ ሂሳቦች እንዲወራረዱ፤ መሰብሰብ የማይችሉትን ደግሞ አጣርተው አስፈላጊውን እርምጃ መወሰድ እንዲሁም ከማን እንደሚሰበሰብ የማይታወቀው ተጣርቶ በማስረጃ እንዲረጋገጥና መሰብሰብ እንዳለባቸው በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

የገቢ ሂሳብ

በገቢ ግብር፤ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ ለመሰብሰብ በሚደነግጉ አዋጆች፣ ደንብና መመሪያዎች መሰረት ሳይሰበሰብ የተገኘ የገቢ ሂሳብ

23.የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብን በሚፈቅዱ ህጎች መሠረት የመንግሥትን ገቢ የሰበሰቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ የገቢዎች ሚኒስቴር እና ጉምሩክ ኮሚሽን ስር ባሉ 11 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር **80,128,846.23** እና በሌሎች በ 15 መ/ቤቶች ብር **6,482,591.17** በድምሩ ብር **86,611,437.40** ገቢ ለመሰብሰብ በሚያስገድዱ አዋጆችና ደንቦች መሠረት ያልተሰበሰበ የገቢ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

24. ገቢ ለመሰብሰብ በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት ገቢ ካልሰበሰቡ መ/ቤቶች መካከል፡- በገቢዎች ሚኒስቴር የምዕራብ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት ብር 40,395,593.81 ፣ የድሬ ዳዋ ገቢዎች ቅ/ጽ/ቤት ብር 16,820,437.20፤ አዳማ ቅ/ጽ/ቤት ብር 6,258,352.17 ሲሆን፤ ከሌሎች መ/ቤቶች ደግሞ ፣ ኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ 4,892,126.44 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

25.በመሆኑም የመንግስት ገቢ ህግና ደንብ በሚፈቅደው መሰረት መሰብሰብ እንዳለበት፣ በተለያዩ ምክንያቶች ያልተሰበሰበው ገቢ እንዲሰበሰብ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ሂሣብ

26. ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች በህግና ደንብ መሰረት የመንግስት ገቢ በወቅቱ እና በአግባቡ መሰብሰባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ዕዳ በ 11 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር **3,858,485,531.48** እና በ 10 ቅ/ጽ/ቤቶች በተለያየ ሂደት የሚገኝ የግብር ዕዳ ብር **9,570,015,663.45** በድምሩ ብር **13,428,501,194.93** ከአንድ ዓመት እስከ 6 ዓመት እድሜ ያለው ውዝፍ እዳ መኖሩን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

27. ውዝፍ ገቢን ካልሰበሰቡ መ/ቤቶች መካከል፡- በገቢዎች ሚኒስቴር የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 4,835,679,269.21፣ በጉምሩክ ኮሚሽን የቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት ብር 2,542,237,409.03፣ የምዕራብ አዲስ አበባ ገቢዎች ቅ/ጽ/ቤት ብር 1,846,488,725.41፣ ምስራቅ አዲስ አበባ ገቢዎች ቅ/ጽ/ቤት ብር 973,477,970.69 እና አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 968,111,114.15 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

28. በመሆኑም የሚሰበሰበው ገቢ መንግስት የሚያከናውናቸውን ማህበራዊና የኢኮኖሚ ልማት አገልግሎቶችን ለማስፋፋት ወሳኝ በመሆኑ የገቢ አሰባሰቡ ትኩረት ተሰጥቶት እንዲሰራ ያልተሰበሰበውም ውዝፍ ገቢ እንዲሰበሰብ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

ተገቢው ማስረጃ ባለመቅረቡ የገቢውን ሂሳብ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ፤

29. የተሰበሰበውን ገቢ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በገቢዎች ሚኒስቴር በ 3 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 27,374,646.70 በግብር ከፋዮች ተቀናሽ የተደረገ የጥገና እና ማሻሻያ ወጪና ልዩ ልዩ ወጪ ትክክለኛ ወጪ ስለመሆኑ ማረጋገጥ ያልተቻለ እንዲሁም በሌሎች 2 መ/ቤቶች ማስረጃ ያልቀረበለት ገቢ ብር 2,407,521.33 በድምሩ ብር 29,782,168.03 ተገቢው ዝርዝር ማስረጃ የቀረበ ባለመሆኑ የገቢ ሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉን ኦዲቱ አሳይቷል፡፡

30. ስለሆነም ማንኛውም ገቢ ማስረጃ ሳይሟላ በገቢ መመዝገቡ ተገቢ ስላልሆነ፣ የገቢ ማስረጃዎች በትክክል ተደራጅተው እንዲያዙና ተገቢው ማስተካከያ እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የተሰበሰበውን ገቢ ለሚመለከተው አካል ገቢ/ፈሰስ ያላደረጉ መ/ቤቶች

31. በፌዴራል መንግስት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3/2003 ክፍል አራት አንቀጽ 13 ተራ ቁጥር 4 በራሳቸው የውስጥ ገቢ ዓመታዊ ወጪያቸውን እንዲሸፍኑ በአዋጅ የተፈቀደላቸው የመንግስት መ/ቤቶች በበጀት ከተፈቀደላቸው በላይ ገንዘብ ከሰበሰቡ ተራፊው ገንዘብ ወዲያውኑ ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት የባንክ ሂሳብ ገቢ ማድረግ አለባቸው በሚለው መሰረት ገቢ መደረጉን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡ በ2 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 94,242,534.74 ፈሰስ መደረጉን የሚያሳይ ማስረጃ በኦዲቱ ወቅት ሊቀርብ ያልቻለ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የተሰበሰበውን ገቢ ለሚመለከተው አካል ፈሰስ ስለመደረጉ ማስረጃ ያላቀረቡ፡- የኢትዮጵያ የምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን ብር 42,695,414.44፣ በቅድስ ጳውሎስ ሆስፒታል የወራቤ ኮምፕርሂንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ብር 51,547,120.30 ናቸው፡፡

32. ስለሆነም ገቢ ያልተደረገው ሂሳብ ፈሰስ ተደርጎ ማስረጃው ሊቀርብ እንደሚገባና ለወደፊቱም በሚሰበሰቡት ሂሳቦች ዙሪያ ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

በመንግስት የጸደቀ የማስከፈያ የዋጋ ተመን (ታሪፍ) ሳይኖር የተሰበሰበ ገቢ፤

33. የመንግስት መ/ቤቶች ከተለያዩ አገልገሎቶች የሚሰብሰቡት ገቢ በመንግስት በጸደቀ የማስከፈያ የዋጋ ተመን መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በ13 መ/ቤቶች ብር 142,237,847.97 የዋጋ ተመን ሳይኖር ገቢ የሰበሰቡ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

34. በመንግስት የፋይናንስ አስተዳደር ደንብና መመሪያ መሠረት በጥናትና በመረጃ የተደገፈ የዋጋ ማስከፈያ ተመን በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል አቅርበው በማጸደቅ ገቢ እንዲሰበስቡ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የወጪ ሂሳብ

35. መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች መሰረት በአግባቡ ወጪ ማድረጋቸውን፣ መጠቀማቸውን፣ ተገቢው ማስረጃ መቅረቡንና ሒሳቡም በትክክል መመዝገቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ

36. በወጪ ለተመዘገቡ ሒሳቦች የተሟላ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በ52 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 307,549,308.13 የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

37. ለወጪዎች የተሟሉ ማስረጃዎች ሳያቀርቡ ወጪ ከመዘገቡ መ/ቤቶች መካከል፡- አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 124,402,770.69፣ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚ/ር ብር 65,817,679.11፣ የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ብር 64,512,008.6፣ በጉሙሩክ ኮሚሽን የሰመራ ቅ/ጽ/ቤት ብር 7,918,972.80፣ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን ብር 5,657,691.03፣ እና የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ብር 4,883,589.49 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

38. ወጪዎች መከፈል የሚገባቸው የተሟላ ማስረጃ ሲቀርብ መሆኑን እና ማስረጃ ላልቀረበላቸው የወጪ ሂሳቦች የተሟላ ማስረጃ እንዲቀርብና ለወደፊቱም የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ የወጪ ሂሳብ እንዳይመዘገብ በየጊዜው ተገቢ ቁጥጥር እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች

39. መሥሪያ ቤቶች የፈጸሟቸው ክፍያዎች በመንግሥት በወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን መሰረት አድርገው የተፈጸሙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ60 መ/ቤቶች ብር **134,289,678.70** ከደንብና መመሪያ ውጭ ያለአግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

40. ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ ክፍያ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል፡- የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ ብር 30,033,442.43፣ የኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ ብር 27,261,848.21፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ብር 11,886,260.93፤ የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን ብር 7,603,012.93፣ የቤተመንግሥት አስተዳደር ብር 6,526,722.02፣ የአርሲ ዩኒቨርሲቲ ብር 6,117,338.86 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

41. መሥሪያ ቤቶች የፈጸሟቸው ክፍያዎች በመንግሥት የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ካልተከተሉ ለመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ከመቻሉም በተጨማሪ ክፍያውን ተዓማኒነት ሊያሳጣው እና በውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ ላይ ክፍተት ሊፈጥር ይችላል። ስለሆነም መሥሪያ ቤቶች በመንግሥት የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ተከትለው ክፍያ መፈጸም እንዳለባቸው እና አለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎችም ተመላሽ መደረግ እንዳለባቸው አሳስበናል።

በየመሥሪያ ቤቶች ለሌሉና ከሥራ ለተሰናበቱ ሰራተኞች የተከፈለ ደመወዝ፤

42. የፌዴራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ተራ ቁጥር 10 የመንግሥት ሠራተኞች የደመወዝ አከፋፈል ደመወዝ ክፍያ ከመፈጸሙ/ወጪ/ ከመደረጉ በፊት መከናወን ካለባቸው ጥንቃቄዎች በተለያዩ ምክንያቶች ከሥራ የለቀቁ ሰራተኞች ከደመወዝ መክፈያ ዝርዝር መውጣት እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡ በመመሪያው መሰረት ስለመፈፀሙ ኦዲት ሲደረግ፡- በ16 መ/ቤቶች ከስራ ለለቀቁ ሰራተኞች ያልሰሩበት ደመወዝ ብር 362,677.16 ክፍያ ፈጽሞ የተገኘ መሆኑ ታውቋል፡፡

43. ከሥራ ለቀው ከሄዱ በኋላ የተፈጸመው የተጣራ ክፍያ ተመላሽ እንዲደረግ፤ ለሥራ ግብርና ለጡረታ ተቀናናሽ ሂሳቦች ደግሞ ተገቢ ማስተካከያ እንዲሰራላቸው እንዲደረግ፤ ሰራተኞች በወሩ ውስጥ ስራ ላይ መገኘታቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከየሥራ ክፍሉ ሳይቀርብ የደመወዝ ክፍያ እንዳይፈጸም በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

<u>በብልጫ (አለአግባብ) የተከፈለ ወጪ</u>

44. መ/ቤቶች የተለያዩ ክፍያዎች ሲፈጽሙ የወጡ አዋጆች፣ ደንብና መመሪያዎችን ተከትለው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በ 52 መ/ቤቶች ለተለያዩ ግንባታና ግዥዎች ብር 3,757,975.53 እና ለውሎ አበልና ለሌሎች ክፍያዎች ብር 19,467,405.15 በድምሩ ብር 23,225,360.68 አለአግባብ (በብልጫ) የተለያዩ ክፍያዎች መፈፀማቸው ታውቋል።

45. ደንብና መመሪያን ሳይከተሉ አለአግባብ የተፈጸሙት ክፍያዎች ተመላሽ እንዲደረጉ፤ ለወደፊቱም የተለያዩ ክፍያዎች ሲፈጸሙ ደንብና መመሪያን መሰረት አድርገው እንዲፈጸሙ በሪፖርታችን አሳስበናል።

<u>የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ያልተከተሉ ግዥዎች</u>

46. የእቃና አገልግሎት ግዥ በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት የተፈፀመ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በ82 መ/ቤቶች ብር 592,454,328.51 የመንግሥትን የግዢ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዢ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

47. ካልተከተሏቸው የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያዎች መካከልም ያለጨረታ በቀጥታ ግዥ በመፈጸም ብር 335, 770,566.81፣ መስፈርቱ ሳይሟላ በውስን ጨረታ የተገዛ ብር 41,750,226.03 ፣ ግልጽ ጨረታ መውጣት ሲገባው በዋጋ ማወዳደሪያ የተፈጸመ ግዥ ብር 112,419,779.61፣ የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ በቀጥታ የተፈጸመ ግዥ ብር 19,049,484.71 እና ሌሎች የግዥ ሂደት ያልተከተሉ ብር 83,464,271.31 እና ብር 1,699,565.00 ከግዥ ኤጀንሲ ፍቃድ ሳይገኝ የተፈጸሙ ግዥዎች ናቸው፡፡

48. ከግዥ አዋጅ፤ ደንብና መመሪያዎች ውጭ ግዥ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል፡- የጉምሩክ ኮሚሽን ዋናው መ/ቤት ብር 66,371,195.74፤ የጂንካ ዩኒቨርሲቲ ብር 61,225,545.74፣ የሰላሌ ዩኒቨርሲቲ ብር 53,071,916.30፣ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አገልግሎት ብር 45, 024, 888.74፣ የአፍሪካ ልህቀት አካዳሚ ብር 36, 216, 480.95 እና የቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ ብር 29,383,900.00 ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

49. ግዥው መንግሥት ባወጣው የግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሠረት መፈጸም እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

በናሙናው መሠረት ገቢ ለመሆኑ በቴክኒክ ኮሚቴ፣ አገልግሎት ለመሰጠቱ በተጠቃሚው ሳይረጋገጥ የተፈፀሙ ክፍያዎች፤

50. ዕቃው ወይም አገልግሎቱ በተፈላጊ ባህሪያት ዝርዝር (Specification) መሰረት መቅረቡን ወይም አገልግሎት ለመስጠቱ በሚመለከተው አካል (ክፍል) መረጋገጥ እንዳለበት በተመለከተው መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በ14 መ/ቤቶች ብር 88,421,062.66 የተገዙ ዕቃዎች በትክክል በተፈላጊ ባህሪያት ዝርዝር (Specification) መሰረት ተገዝቶ ለመቅረቡ በቴክኒክ ኮሚቴ ሳይረጋገጥ ወይም አገልግሎቱ ለመሰጠቱ በተጠቃሚው ሳይረጋገጥ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ ታውቋል።

51. ማንኛውንም የዕቃ ግዥ ተፈጽሞ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ ከመደረጉ በፊት በተፈላጊ ባህሪያት ዝርዝር (Specification) መሰረት ተገዝቶ ለመቅረቡ በቴክኒክ ኮሚቴ (በባለሙያ) ወይም አገልግሎት ለመስጠቱ በሚመለከተው አካል (ክፍል) መረጋገጥ ስላለበት ለወደፊቱ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለባቸው አሳስበናል።

ንብረቱ ገቢ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብ ሂሳቡ በወጪ የተመዘገበ

52. የመንግስት ገንዘብ ወጪ ሆኖ የተገዛው ንብረት ለመ/ቤቱ ገቢ ለመሆኑ የንብረት ገቢ ደረሰኝ የተቆረጠለት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በ14 መ/ቤቶች በድምር ብር 42,658,268.18 ንብረቱ ገቢ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብ ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

53. የመንግስት ገንዘብ ወጪ ሆኖ የተገዛው ንብረት ለመ/ቤቱ ገቢ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብ ሂሳቡን በወጪ ከመዘገቡ መ/ቤቶች መካከል የነዳጅና የኢነርጂ ባለስልጣን ብር 25,452,996.60፣ የኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ ብር 10,706,509.24 እና የጉምሩክ ኮሚሽን ዋናው መ/ቤት ብር 4,100,000.00 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

54. መ/ቤቶች በዚህ መልኩ ወጪ ለሆነው ሂሳብ ንብረቱ ገቢ ለመደረጉ የንብረት ደረሰኝ እንዲቀርብ አሳስበናል፡፡

በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ

55. በበጀት ዓመቱ በመንግስት መ/ቤቶች በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ ደንብና መመሪያን ተከትሎ የተፈፀመ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በ9 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 28,623,796.06 በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ ተመዘግቦ ተገኝቷል፡፡

56. የመንግስት ሂሳብ አያያዝ ስርዓት በሚያዘው መሰረት የሂሳብ ማስተካከያ በመስራት የቅድሚያ ክፍያው በተሰብሰቢ ሂሳብ እንዲመዘገብ እና ለወደፊቱም የሂሳብ ምዝገባ በመንግስት ደንብና መመሪያ መሠረት እንዲፈጸም ተገቢ ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

የሂሳብ መደቡን ሳይጠብቅ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ ሂሳብ

57. የመንግስት መስሪያ ቤቶች በበጀት አደረጃጀት ሥርዓት መሠረት የተፈቀደላቸው በጀትና የወጣውን ወጪ በሚያሳይ መልኩ ተለይቶ በተሰጠ የበጀት መለያ መደብ ተጠቅመው የሂሳብ እንቅስቃሴያቸውን መመዝገባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በ99 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 432,320,927.40 የወጪ ሂሣብ መደባቸውን ሳይጠብቁ ተመዝግበው ተገኝቷል፡፡

58. በመሆኑም ለወደፊቱ ተመሣሣይ የአሠራር ግድፈት እንዳይፈፀም ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

የተከፋይ ሂሣብ

በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ

59. ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ እየተከፈሉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በ92 መ/ቤቶች ብር **1,961,987,326.07** በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

60. የተከፋይ ሂሳቡ በዕድሜ ቆይታ ጊዜው ሲተነተን፡- ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ብር 732,397,345.07፣ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ብር 732,384,618.24፣ ከአምስት ዓመት እስከ አሥር ዓመት ብር 160,614,513.85 እና ከአሥር ዓመት በላይ ብር 40,263,415.82 ሲሆን፣ ቀሪው ሂሳብ ብር 296,327,433.09 የቆይታ ጊዜው በግልጽ ያልታወቀ ነው፡፡

61. በተጨማሪም በ2 መ/ቤቶች ከ1 ወር እስከ 5 ዓመት የቆየ ብር 1,324,076.72 በወቅቱ ያልተከፈለ የፕሮጀክት የተከፋይ ሂሳብ የሚገኝ መሆኑ ታውቋል፡፡

62. በመሆኑም የተመለከተው ውዝፍ ተከፋይ ሂሳብ ተጣርቶ በፋይናንስ ህጉ መሰረት ለሚመለከታቸው አካላት እንዲከፈል በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

<u>በተከፋይ ሂሳብ የተመዘገበና ዝርዝር ማስረጃ ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ</u>

63. የተከፋይ ሂሳቦች በተገቢ ማስረጃ ተደግፈው የተያዙ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ16 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 1,888,659,402.28 በተከፋይ የተመዘገበ ቢሆንም መቼ በተከፋይነት እንደተመዘገበ፣ ተከፋይ ሂሳቡ ለማን እንደሚከፈል የማይታወቅና የቆይታ ጊዜዉን የሚገልፅ ማስረጃ የሌለ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

64. የተከፋይ ሂሳብ መነሻ ማስረጃ ካልያዙ መ/ቤቶች መካከል፡- የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ብር 1,013,809,299.24፣ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ብር 583,614,102.50፣ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ብር 131,833,508.57 እና የጉምሩክ ኮሚሽን ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት ብር 96,565,062.58 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

65. ማስረጃ ላልቀረበላቸው ተከፋይ ሂሳቦች ተገቢው ማስረጃ እንዲቀርብ እና ትክክለኛነቱ እንዲረጋገጥ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

<u>የበጀት አጠቃቀም</u>

66. መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀትና በሥራ ላይ ያዋሉት ሂሳብ ሲመዛዘን ከበጀት በላይ ወጪ የተደረገና በርካታ ያልተሠራበት በጀት የተገኘ ሲሆን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

<u>ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ</u>

67. መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- በ 35 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች በደንቡ መሠረት ሳያስፈቅዱ ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የሆነ ሂሳብ ከመደበኛ በጀት ብር 1,205,325,855.45፣ ከውስጥ ገቢ ብር 118,570,797.33 እና ከካፒታል በጀት ብር 244,094,832.83 በድምሩ ብር 1,567,991,485.61 ተገኝቷል፡፡

68. ለሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ ካደረጉ መ/ቤቶች መካካል፣ ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ብር 358,685,288.01፣ ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ብር 166,729,110.97፣ ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 139,915,215.52፣ ዲላ ዩኒቨርሲቲ ብር 125,060,012.20 እና አርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ ብር 113,211,497.42 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

69. በጀት ሳይፈቀድ ወጪ ማድረግ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ የተከለከለ ከመሆኑ በላይ የመንግስት ገንዘብ አላግባብ እንዲባክንና በጀት ለማጽደቅ ስልጣን የተሰጠው አካል ሳይፈቅድ የመንግስት ገንዘብ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡በመሆኑም ለወደፊቱ መ/ቤቶቹ የበጀት ዝግጅታቸውም በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ መዘጋጀት እንዳለበትና አፈጻጸሙ የበጀት አዋጅን ተከትሎ እንዲሆን በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

ስራ ላይ ያልዋለ በጀት

70. መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት በጀታቸውን በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋላቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት ከ10% በላይ ያልተጠቀሙበትን ብቻ በመውሰድ በ136 መ/ቤቶች መደበኛ በጀት ብር 5,867,146,616.99፣ የውስጥ ገቢ ብር 368,505,440.17 እና ካፒታል ብር 28,840,316,795.15 በድምሩ ብር 35,075,968,852.31 ስራ ላይ ያልዋለ በጀት ተገኝቷል፡፡

71. ስራ ላይ ያልዋለ በጀት ከተገኘባቸው መ/ቤቶች፡- የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ብር 8,958,885,180.79፣ ገንዘብ ሚኒስቴር ብር 6,394,497,991.96፣ የጤና ሚኒስቴር ብር 3,106,014,366.16፣ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ብር 1,202,419,072.23፣ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ብር 1,095,090,681.00፣ ትምህርት ሚኒስቴር ብር 915,115,768.98 እና ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ብር 599,184,493.26 ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

72. በጀት ከተፈቀደ በኋላ አለመጠቀም የታቀዱ ሥራዎች ሳይከናወኑ ሊቀሩና መ/ቤቱም ዓላማውን እንዳያሳካ ሊያደርግ ስለሚችል፣ ለወደፊቱ በበጀት ዝግጅትና አጠቃቀም ላይ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

የንብረት አያያዝና አጠባበቅ

የቋሚ እና አላቂ ዕቃዎች አስተዳደር ድክመቶች

73. መ/ቤቶች የመንግሥትን ንብረት በደንቡ መሠረት መዝግበው ቁጥጥር የሚያደርጉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት የአሰራር ድክመቶች በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

የግኝቶች መግለጫ	መ/ ቤቶች
ለቋሚ ዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ	19
በየስራ ክፍሉ ለተሰጡ የቋሚ ዕቃዎች መቆጣጠሪያ ካርድ (User Card) ያላዘጋጁ	8
የአላቂ ዕቃዎች መቆጣጠሪያ ስቶክ/ ቢን ካርድ ያላዘጋጁ ወይም የተሟላ ምዝገባ ያላደረጉ	33
ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ	19
የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ዓመታዊ ቆጠራ ያላደረጉ	23
ቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ ወይም የተሟላ ምዝገባ ያላከናወኑ	9
ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው	73
አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመመሪያው መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው	111
ተያያዥነት ያላቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሰው ተደርበው የሚከናወኑባቸው	22
ከመ/ቤቱ ከስራ የለቀቁ ሰራተኞች(ኃላፊዎች) ሲጠቀሙበት የነበሩ ንብረቶች ወደ ግምጃ ቤት ተመላሽ እንዲሆን ያላደረጉ	19
የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፈበት መድኃኒትና የተለያዩ ኬሚካሎችን በአግባቡ ያላስወገዱ	21
የተተዉ፣ የተወረሱ እና ያልተወረሱ በህግ ሂደት ላይ ያሉ ንብረቶች አስተዳደር እና ቁጥጥር ሂደት ላይ የሚገኙ	13*
ተያዥ/ዋስትና ያላቀረቡ ሰራተኞች ያሉባቸው	12
የቋሚና አላቂ ዕቃዎች በአንድ ላይ እንዲቀመጡ ያደረጉ	4/3*
በእርዳታና በስጦታ ለተገኙ ዕቃዎች ዋጋ ያልተመኑ	4

መፍቻ:- *-ቅ/ጽ/ቤት

74. መንግሥት ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች ግዥ በየዓመቱ የሚያወጣው ወጪ ከፍተኛ ቢሆንም በብዙ መ/ቤቶች የሚታየው የንብረት አስተዳደር አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት በእነዚህ መ/ቤቶች የተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ደካማ በመሆኑ ዕቃና ንብረት ለምዝበራና ብክነት የመጋለጥ እድሉ ከፍተኛ ነው፡፡

75. አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ንብረቶች ያለአገልግሎት በየንብረት ክፍሉ ተከማችተው እያሉ ተመሳሳይ ንብረቶች ግዥ የሚፈጽሙ መ/ቤቶችም መኖራቸው በኦዲታችን ወቅት ታውቋል።

76. በመሆኑም የንብረት አስተዳደር ስርዓቱ በመንግስት ንብረት አስተዳደር ህግ መሰረት እንዲፈፀም እና የቁጥጥር ስርዓቱ እንዲጠናከር በላክነው ሪፖርት አሳስበናል ፡፡

<u>የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝ</u>

77. የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝን በተመለከተ በ2014 በጀት ዓመት በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሚከተሉት ግድፈቶች ተገኝተዋል፡፡

የግኝቶች መግለጫ	የተሽከሪካሪዎች ብዛት		
	የመ/ ቤቶች	መኪና	ሞተር ብስክሌቶች /ሌሎች
ሊብሬ ያልቀረበላቸው	23	188	4/1
ያለአገልግሎት ወይም በብልሽት የቆሙ ተሽከርካሪዎች የተገኙባቸው መ/ቤቶች	60	694	56/1
የሰሌዳ ቁጥር የሌለው	1	1	
ሻንሲ ቁጥር የሌላቸው	3	3	
የሞተር ቁጥር የሌላቸው	2	5	
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌሎች መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሥም የሆነ	25	275	
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተርና በተሽከርካሪዎቹ ላይ በተመለከተው ሞተር ቁጥር መካከል ልዩነት ያለ መሆኑ	3	3	
የነዳጅ መቆጣጠሪያቸው/ጌጅ/ የማይሰራ	9	44	
ሊብሬው ኖሮ ተሽከርካሪው በአካል የሌለ	2	1	4
አገልግሎት የማይሰጡ/መወገድ/ ያለባቸው ተሽከርካሪዎች	3	5	
የመድን ዋስትና ያልተገባላቸው ተሽከርካሪዎች	1	10	

<u>መፍቻ</u>፡- ሌሎች ማለት- ሎቤድ፣ትራክተር፣ ባጃጅ የመሳሰሉት ናቸው፡፡

78. በመሆኑም በብልሽት ምክንያት ቆመው የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልገሎት መስጠት እንዲችሉ፣ ተጠግነው ማገልገል የማይችሉት ደግሞ በመንግሥት ንብረት አስተዳዳር መመሪያ መሠረት እንዲሸጡ/እንዲወገዱ፣ ሊብሬ እና ሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው እንዲወጣላቸው፤ የንብረት አስተዳደር ስርዓቱ በመንግስት ንብረት አስተዳደር ህግ መሰረት እንዲፈፀም እና የቁጥጥር ስርዓቱ እንዲጠናከር በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ፋይናንሲንግና የፍሃዊነት መሰረታዊ አገልግሎት ለሁሉ ዓቀፍ የእድገት ተጠቃሚነት ፕሮግራም ኦዲትን በተመለከተ

79. የኢትዮጵያ መንግሥትና የዓለም ባንክ ባደረጉት ስምምነት መሠረት የፍትሃዊነት መሠረታዊ አገልግሎት ለሁሉ ዓቀፍ የዕድገት ተጠቃሚነት ፕሮግራም (Enhancing Shared Prosperity through Equitable Service-ESPES) የተከታታይ እና የማረጋገጫ ኦዲት የአገልግሎቱ አቅራቢ በሆኑ በወረዳና በክልል ደረጃ በሚገኙ የጤና ፣የትምህርት፣ የግብርናና ተፈጥሮ ሃብት፣ የንፁህ ውሃ አቅርቦትና የገጠር መንገድ ሴክተሮች እየተከናወነ የተከታታይ ኦዲት በየሩብ ዓመቱ፣ የማረጋገጫ ኦዲት ደግሞ በገንዘብ ሚኒስቴር በተጠየቀ ጊዜ እየተከናወነ በስምምነቱ መሠረት ሪፖርቱ ለገንዘብ ሚኒስቴር እና ለዓለም ባንክ በወቅቱ እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

80. በዚሁ መሰረት በበጀት ዓመቱ 265 የተከታታይ፣ 50 የማረጋገጫ (Verification) እና 1 ዓመታዊ ማጠቃለያ ጠቅላላ ድምር 316 ኦዲቶችን ለመሥራት የታቀደ ሲሆን በበጀት ዓመቱ አፈጻጸሙም 276 የተከታታይ ኦዲት፣ 113 የማረጋገጫ (Verification) እና 1 ዓመታዊ ማጠቃለያ በጠቅላላ ድምር 390 (123.41%) ኦዲቶችን ማከናወን ተችሏል፡፡

81. በተጨማሪም በገንዘብ ሚኒስቴር በኩል በለጋሽና አበዳሪ ድርጅቶች የበጀት ግልፀኝነት ማረጋገጫ ኦዲት እንዲደረግ በተጠየቀው መሠረት ከክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች ጋር በጋራ ለመሥራት በተደረሰው ስምምነት በመ/ቤታችን ለኦዲቱ የወጣውን ወጪ በመሸፈን በአ/አበባ ከተማ ዋና ኦዲተር መ/ቤት 17፣ በኦሮሚያ ክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤት 68፣ በሲዳማ ክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤት 3፣ በደቡብ ክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤት 55 እና በአማራ ክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤት 34፣ በድምሩ 177 ወረዳዎችን እና ከተማ አስተዳደሮች የበጀት ግልጸኝነት ኦዲት ተከናውኗል፡፡

የመንግሥት አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሳብ ኦዲትን በተመለከተ

82. በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ከገንዘብ ሚኒስቴር በተላከው የ2014 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት አጠቃላይ የገቢና የወጪ ዝርዝር መግለጫ ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ገቢና ወጪ፣ ሀብትና ዕዳ እንዲሁም የመንግሥት ገንዘብ ነክ የሆኑ መረጃዎችን ኦዲት በማድረግ ሪፖርቱ ለሚመለከታቸው አካላት ተልኳል፡፡

የልዩ ኦዲት ስራዎች

83. በዕቅድ ከያዝናቸው የኦዲት ሥራዎች በተጨማሪ በኦዲት ዓመቱ በተለያዩ አካላት ከተጠየቁት ልዩ ኦዲቶች ቅድሚያ የተሰጣቸውን 8 ኦዲቶች ለማከናወን ታቅዶ አፈፃፀሙ 11 ልዩ ኦዲቶች የኦዲት ሥራ ተጠናቀው ሪፖርቱ ለሚመለከታቸው አካላት ተልኳል፡፡

የፌደራል መንግስት ለክልሎች የሰጠውን ድጎማ የኦዲት ሪፖርት በተመለከተ

84. የፌዴራል መንግስቱ ለክልል መንግስታት የሚሰጠውን የበጀት ድጋፍና ልዩ ድጎማዎችን ኦዲት የማድረግ ሥልጣን በህገመንግስቱ አንቀጽ 94/2 እና በአዋጅ ቁጥር 982/2008 እንደተሻሻለው 1146/2011 አንቀጽ 5 ንኡስ አንቀጽ 16 ለፌዴራል ዋና ኦዲተር የተሰጠ እና ለክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤቶችም ተመሳሳይ ስልጣንና ኃላፊነት የተሰጣቸው በመሆኑ ይህን ለማስፈጸም እና የውጭ ኦዲት ድግግሞሽን ለማስቀረት የነጠላ ኦዲት አዋጅ ቁጥር 1251/2013 መሰረት በማድረግ የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 2/2014 ከክልሎች ጋር በመሆን እንዲወጣ ተደርጎ ለመጀመሪያ ጊዜ በአራት ክልሎች በዚሁ በጀት አመት የኦዲት ሥራው እንዲጀመር ተደርጓል፡፡

85. በዚሁ መሰረት በ ኦሮሚያ ክልል 461 መ/ቤቶች፣ በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል 122 መ/ቤቶች፣ በ ሲዳማ ክልል 42 መ/ቤቶች እና በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር 13 ፕሮጀክቶች ላይ የነጠላ ኦዲት ተከናውኖ ሪፖርቱ ለመ/ቤታችን ቀርቧል፡፡ የኦዲቱ ግኝቶች ላይ እያንዳንዱ ክልልሎች በተሰጣቸው ኃላፊነት መሰረት አስፈላጊውን ማሻሻያ እንዲያደርጉ አሳስበናል፡፡

የተከበሩ አፈ ጉባዔ!

የተከበሩ ም/አፈ ጉባዔና

የተከበሩ የመንግስት ወጪ አስተዳደር ቁ/ጉ/ቋ/ኮ/ሰብሳቢ

የተከበራችሁ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት!

ክቡራትና ክቡራን!

<u>የክዋኔ ኦዲት አፈጻጸምና ዋና ዋና ግኝቶችን በተመለከተ፣</u>

86. መ/ቤታችን ከፋይናንስና የሕጋዊነት (Regularity) ኦዲት በተጨማሪ በክዋኔ ኦዲት ላይ ትኩረት ለማድረግ ባስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት በሶስት የክዋኔ ኦዲት ዳይሬክቶሬት እና አንድ የአካባቢ ኦዲት ዳይሬክቶሬት በድምሩ በ4 ዳይሬክቶሬት 23 ቡድን በማደራጀት በመንግሥት መ/ቤቶች የተቀረፁ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች፣ እንዲሁም ለተልዕኮ ማስፈፀሚያ የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋላቸውን እና የታለመላቸውን ዓላማና ግብ በብቃትና ስኬታማ በሆነ መንገድ ማሳካታቸውን እና የአካባቢ ጥበቃና የዘላቂ ልማት ግቦችን ሊያሳካ በሚችል መልኩ ማከናወናቸውን ለማረጋገጥ በመጋቢት 2014 ተጀምረው እስከ ጥር 30/2015 የሚጠናቀቁ 23 አዳዲስ የክዋኔ ኦዲቶችና አንድ የዞረ እና 7 የክትትል ኦዲቶችን ለማከናወን በድምሩ 31 ኦዲቶች በእቅድ ተይዘው ነበር፡፡

87. በዚህም መሠረት አንድ የዞረውና 23 አዲስ ክዋኔ ኦዲቶች እና 8 የክትትል ኦዲቶች በድምሩ የ32 ክዋኔ ኦዲቶች ሥራ በታቀደው መሠረት ተከናውኗል፡፡ በዓመቱ የክዋኔ ኦዲት የእቅድ ክንዉን 103.22% ሆኗል፡፡ የተጠናቀቁት ሪፖርታቸው ለም/ቤቱና ለሚመለከታቸው አካላት ተልከዋል፡፡ ከተሰሩት የክዋኔ ኦዲቶች ዉስጥ አምስቱ አካባቢ ኦዲት ላይ ያተኮሩ ሲሆን፣ ሌሎቹ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ እና የሴቶችን አሳታፊነትና እኩል ተጠቃሚነት እንዲሁም ዘላቂ ልማት ግቦችን ባካተተ መልኩ ኦዲቱ የተከናወነ ሲሆን የምክር ቤቱን ትኩረት የሚሹ ዋና ዋና ግኝቶቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

<u>በኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን የአዋሽ መልካሳ ኬሚካል ፋብሪካ የሥራ አፈጻጸም እና የአካባቢ አያያዝ ሥርዓት ውጤታማነትን በተመለከተ፣</u>

88. የፋብሪካው የፕሮፎርማ ግዥዎች የመንግስት ግዥ መመሪያን እና የኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን የግዥ መመሪያ ቁጥር 07/2012 ያልተከተሉ መሆኑ፤ እንዲሁም ለምርት አገልግሎት የሚውሉ የግብዓት ግዥዎችን ሲፈፅም ዝርዝር የግዥ ዕቅድ የሌለውና በተፈለገው ጊዜ፣መጠን፣ጥራት እና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ያልተከናወኑ መሆናቸው፣ ለአብነትም ብዛታቸው 29,950 ኪ.ግ የሚሆኑ የተለያዩ ኬሚካሎች በብር 18,866,336.86 ከዉጭ ተገዝተው መጥተው የመጠቀሚያ ግዜአቸው አልፎባቸዉ ያላገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፣

89. ፋብሪካው ነባር ፋብሪካዎችን መልሶ የማቋቋም እና የሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ ፋብሪካ የግንባታ ፕሮጀክቶች ኮንትራት ውሉ ላይ በተቀመጠው መስፈርት /Specification/ እና በውል ሰነዱ የጥራት ስታንዳርድ መሰረት በተያዘላቸው በጀት እና ጊዜ ተገንብተው ወደ ምርት ማምረት ሂደት ያልገቡ መሆኑ፡፡ በዚህም ምክንያት የሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ ፋብሪካ የግንባታ ፕሮጀክት ውል ከተገባው የ86,243,291.06 ወይም 60.68% ጭማሪ ወጪ ያስከተለ መሆኑ፣

90. ፋብሪካው ምርታማነቱን በማሳደግ የአልሙኒየም ሰልፌት፣ ሰልፈሪክ አሲድ እና ሃይድሮጅን ፐርኦክሳይድ ኬሚካል ምርቶች በሶስት አመት (ከ2012-2014 ዓ.ም) ሊደርስበት ከሚችለው የማምረት አቅም (Attainable Design Capacity) ልክ (30,308 ቶን) ባለማምረቱ ብር 277,996,009.60 ማግኘት የነበረበትን ገቢ ያላገኘ መሆኑ፣

91. ፋብሪካው የአከባቢ አስተዳደር ስርዓትን በመዘርጋት የደረቅ እና የፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እንዲሁም የአየር ብክለት መከላከል ስራዎችን በአግባቡ ያልሰራ መሆኑ፤

በኦዲቱ ታይቷል፡፡

<u>በኢትዮጵያ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ አጓጓዝ፣ አወጋገድ እና የፕላስቲክ ምርቶች ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር ስርዓት ውጤታማነትን በተመለከተ</u>

92. ባለስልጣኑ የፕላስቲክ ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር እንዲሁም ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ አጓጓዝ፣ አወጋገድ እና የቁጥጥር ስርዓት ውጤታማነት በተመለከተ ዘርፉ ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች፣ ከክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣

93. የኦዲት ቡድኑ በሐረር፣ ሃዋሳ፣ ጭሮ፣ አዳማ፣ ሞጆ፣ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሻሸመኔ ከተሞች ባደረገው የመስክ ምልከታ እና በባለስልጣኑ በተደረገ የክትትል ሪፖርት በባህርዳር፣ ደሴ ፣ጎንደር እና ቦንጋ ማስረጃዎች መሰረት የሚገኙ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች ዘመናዊ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች (Sanitery land fill) ሳይሆኑ ክፍት ስፍራ ላይ የሚገኙ፤ የሚበሰብሱ እና የማይበሰብሱ ቆሻሻዎች ተለይተው ያልተቀመጡባቸው መሆኑ ፣ ቆሻሻው በአግባቡ የማይጣል በመሆኑ እሳት የሚያስነሱ መሆናቸው፣ ከህብረተሰቡ መኖሪያ ቤቶች ተገቢውን ርቀት ያልጠበቁ መሆኑ፣ ከቆሻሻዎቹ የሚመነጩ መርዛማ ፍሳሾች በአካባቢው በሚገኙ የወንዝ ተፋሰሶች ጋር የሚቀላቀሉ መሆኑና በወንዙ መስኖ የሚጠቀሙ ገበሬዎች የሚያመርቱትን ምርት የሚጠቀሙ ማህበረሰቦች እና በየቦታው ከተጣሉ ቆሻሻ የሚበሉ እና ከወንዙ የሚጠጡ እንስሶች መኖራቸው፣

94. በአዲስ አበባ ከረጲ ቆሻሻ ማስወገጃ ክፍት ስፍራ አጠገብ ረጲ ኤሌክትሪክ ማመንጫ በ2012 ዓ.ም ጀምሮ ከቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች ብረቶች፣ ማይካ ኤሌትሮኒክስ፣ ሀይላንዶች እንዲለዩ በማድረግ ፌስታሎችን ከሚበሰብስ ቆሻሻ ጋር ኤሌትሪክ የማመንጨት ስራ የሚከናወን ሲሆን ፕሮጀክቱ ሲቋቋም በሰዓት 50 ሜጋ ዋት ለማምረት የተጠና ቢሆንም ከ3 ወር በፊት 13 ሜጋ ዋት ብቻ ያመርት እንደነበረ ነገር ግን ኤሌክትሪክ ማመንጨት ካቆመ 3 ወር የሆነው መሆኑ፤ ሆኖም ይህንን በተመለከተ በባለስልጣኑ የሚደረግ ክትትልና ድጋፍ አለመኖሩ፣

95. ባለስልጣኑ ውፍረታቸው 0.03 ሚሊ ሜትርና ከዚያ በታች ሆነው በስብሰው ከአፈር ጋር የማይዋሃዱ የፕላስቲክ ምርቶችን ተለይቶ ከተቀመጠ አገልግሎት በቀር ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡ ወይም በአገር ውስጥ እንዳይመረቱ ተከታታይነት ባለው መልኩ ክትትል በማድረግ ዘገባ ያላዘጋጀ መሆኑ እና ባደረጋቸው ክትትሎችም ከህግ ውጪ ሰርተው በተገኙ ድርጅቶች ላይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እርምጃ እንዲወሰድ ያላደረገ መሆኑ፣

96. ባለስልጣኑ የአገልግሎት ዘመናቸው አጭር የሆኑ የፕላስቲክ ምርቶችን የሚያመርቱ አምራቾች በጊዜ ሂደት ሙሉ ለሙሉ ምርቱን የሚያቋርጡበትን እና በሌሎች ተተኪ ምርቶች የሚለውጡበትን እንዲሁም ያመረትዋቸው ምርቶች ጥቅም ላይ ከዋሉ በኃላ የሚሰበስቡበትና መልሰው ጥቅም ላይ የሚውሉበት አሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላገረገ መሆኑ፣

97.ባለስልጣኑ ማንኛውም ተፅዕኖ ሊያስከትል የሚችል የልማት ፕሮጀክቶት ባለቤት ወደ ትግበራ ከመግባቱ በፊት የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ በማካሄድ ከሚመለከተው የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤት ፈቃድ ማግኘቱን እንዲሁም በሚመለከታቸው የዘርፍ መ/ቤቶች የተሰጡ የአካባቢና የማህበረሰብ ተጽዕኖ ግምገማ የይሁንታ ፈቃዶች በህጉ መሠረት እየተገበሩ መሆናቸውን ያላረጋገጡ መሆኑ በኦዲቱ ታይቷል፡፡

<u>በኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን የኢንዱስትሪ ፓርኮች የተቀናጀ የደረቅ እና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ውጤታማነትን በተመለከተ፣</u>

98. ኢንዱስትሪ ፓርኮች ሲቋቋሙ የተጠናላቸው የአካባቢያዊ እና የማህበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ (ESIA-Environment and Social Impact Assessment) ጥናት አንድ ማዕከላዊ ጥናት ማለትም ለቴክስታይልና ጋርመንት ዘርፍ ብቻ ሲሆን፣ ጥናቱ የማያካትታቸው ዘርፎች- የቀለም ፋብሪካ፣ ማዳበሪያ (የሲሚንቶ ከረጢት) ማምረቻ፣ ፕላስቲክ (ለታሸገ ውሃ ግብአት) የሚሆን ማምረቻ፣ የመሳሰሉት ድርጅቶች የአካባቢያዊ እና የማህበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት ሳይጠናላቸው በኢንዱስትሪ ፓርኮቹ የማምረት ስራ ጀምረው እየሰሩ ያሉ መሆኑ፣

99. በኢንዱስትሪ ፓርኮች ከፍሳሽ ማጣሪያ የሚገኝ ዝቃጭ (በተለይ በሐዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ) ለረጅም ጊዜ በፓርኩ ግቢ ውስጥ ለዝናብ በተጋለጠ ሁኔታ ከ5 ዓመታት በላይ ተከማችቶ የሚገኝና በዝናብ ወቅትም እየታጠበ ከዝናብ ፍሳሽ ጋር በመቀላቀል የግቢውን ውበት እያበላሸ መሆኑ፣

100.በአዳማ ኢንዱስትሪ ፓርክ እና በቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ ስር የሚገኙት ፋብሪካዎች ፍሳሻቸውን ወደ አካባቢው ማህበረሰብ የሚለቁ መሆናቸው እና በተለይ በቦሌ ለሚ የሚገኘው ፋብሪካ ፍሳሹ ወደ ማሳ (እርሻ) የሚገባ እና ከማጣሪያውም መጥፎ ሽታ የሚወጣ መሆኑ፣

101.ደብረ ብርሃን እና ባህር ዳር ኢንዱስትሪ ፓርኮች የፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ ግንባታ ስራዎች በኮርፖሬሽኑ አመታዊ ዕቅድ ማለትም በ2013 ዓ.ም እና በ2014 ዓ.ም 100% ለማጠናቀቅ ዕቅድ የተያዘ ቢሆንም፣ በተያዘው ዕቅድና በወቅቱ ተጠናቀው ወደ ስራ ያልገቡ መሆኑ፣

102. ኮርፖሬሽኑ ለፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ ያወጣው ወጪ ከባለሃብቶች ለፍሳሽ ማከሚያ ከሰበሰበው ገቢ ጋር ሲነፃፀር፤ለፍሳሽ መጣሪያ ከፍተኛ ወጪ እያወጣ መሆኑ፤ ለማሳያ-ከ2012ዓ.ም እስከ 2014 ዓ.ም ድረስ ብቻ ብር 404,932,948.88 ወጪ ያደረገ ሲሆን ከባለሃብት የሰበሰበው ገቢ ግን በብር 1,820,674.33 እንዲሁም በዶላር 2,812,672.12 ብቻ በመሆኑ ኮርፖሬሽኑ ከፍተኛ ወጪ እያወጣ መሆኑ በኦዲቱ ታይቷል፡፡

<u>በግብርና ሚኒስቴር የአበባ እርሻ ልማት ምርታማነት እና የአካባቢ አያያዝ ሥርዓት ውጤታማነትን በተመለከተ</u>

103. የአበባ እርሻ በአከባቢው ላይ ጉዳት እንዳያደርስ እና የዘርፉ ግብይት የሚመራበት የራሱ የሆነ የህግ ማዕቀፎች(ፖሊሲ፣ አዋጆች፤ ደንብና መመሪያዎች) እንዲሁም የኮንሶሊዴሽን(consolidation) የህግ ማዕቀፎች፣ የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ የህግ ማዕቀፍ፤ የአከባቢ ስነ-ምግባር ደንብ መሰረት መመሪያ እና ማኑዋል ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፤

104. የአበባ እርሻ ልማት ላይ የተሰማሩ በናሙና የታዩ ድርጅቶች የሚጠቀሟቸው ግብአቶች ማለትም ኬሚካል፣ ፍሳሽ ቆሻሻ፣ ተረፈ-ምርት፣ የኬሚካል መያዣ ፕላስቲኮች እና ፍሳሽ ቆሻሻ፣ የመሳሰሉት ያለምንም ቅድመ ማጣራት ወደ አከባቢው ማህበረሰብ የሚለቀቁ መሆናቸው፤ እንዲሁም የሚጠቀሙት ፀረ-ተባይና ፀረ-አረም ኬሚካሎች ወደመሬት ሰርጎ በመግባት መሬቱን እንዳይመርዝ የፕላስቲክ ንጣፍ የማይጠቀሙ በመሆናቸው በአፈሩ እና አካባቢው ላይ ጉዳት እየደረሰ መሆኑ፣

105. የአበባ እርሻ ድርጅቶች የሚጠቀሙት የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችና ግብዓቶች ወደ ሀገር ውስጥ ሲገቡ የአግሮ ኬሚካሎች መጠን ፍላጎትን መሰረት ባደረገ መልኩ እንዲገዛና እንዲሰራጭ፣ ግልጽነት ያለው የማበረታቻ ሥርዓት እንዲዘረጋ ያላደረገ መሆኑ ፤ እንዲሁም ግብዓቶች በጉምሩክ በኩል እንዲገቡ የፈቃድ ወረቀት ከመስጠት ውጪ ያስገቡት ግብአት ከምን ያክል ቆይታ በኋላ አገልግሎት አይሰጥም የሚለውንና የገባውም ግብአት ስለትክክለኛነቱ እንደማያረጋግጡና ተመዝግቦ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባም ክትትልና ቁጥጥር ያላደረገ መሆኑ፣

106. የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች የአወጋገድ መመሪያ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ባለማድረጉ በአበባ እርሻ ድርጅቶች ውስጥ የሚገኙ ጊዜ ያለፈባቸው ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ከሚመለከተው አካላት ጋር በመሆን እንዲወገድ ባለማድረጉ ድርጅቶቹ ውስጥ ተከማችተው ሳይወገድ ብዙ ጊዜ በመቀመጡ ለአካባቢ፣ ለሰው፣ ለእንስሳትና ለውኃ አካላት ደህንነት አስጊ መሆኑ፤

107. የአከባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር 299/1995 ዓ.ም ማንኛውም ፕሮጀክት ኢንቨስትመንት ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት ሁሉም የአከባቢ ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ (ESIA) እንዲያዘጋጁ የሚል አስገዳጅ አዋጅ የወጣ ሲሆን ሁሉም የአበባ እርሻ ድርጅቶች ከ1996 በኋላ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ቢሆንም የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ሳያዘጋጁ ወደ ስራ የገቡ ሲሆን፣ እንዲሁም አንዳንድ የአበባ እርሻ ድርጅቶች ደግሞ የአከባቢ አያያዝ ዕቅድ(Environmental management plan) ማዘጋጀት ሲገባቸው ያላዘጋጁ መሆኑ፣

108. አንዳንድ የአበባ እርሻ ድርጅቶች ሀገራዊና እና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች፣ የስራ አካባቢ የደህንነት መጠበቂያ ቁሶች፤ የጤና ምርመራ ድንጋጌዎች መሰረት አሟልተው እየሰሩ አለመሆናቸው፤

109. የደረቅ እና የፈሳሽ ቆሻሻ አያያዝ፣ አከመቻቸት እና አወጋገድን በተመለከተ የፍሳሽ ማጣሪያ/ማከሚያ ቴክኖሎጂዎች ዊትላንድ የማይጠቀሙና እንዲሁም ደረቅ ቆሻሻን ለማስወገድ ደረቅ ቆሻሻው ከምንጩ ተለይተው በደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ገንዳዎቹ ላይ የጽሁፍ/ምልክት የማይፃፍበት እና ደረቅ ቆሻሻው የሚቃጠልበት የተለየ ቴክኖሎጂ ኢንሲኔሬተር(incinerator) የሌለውና ቆሻሻው ግቢ ውስጥ ተጠራቅሞ ክፍት ቦታ ላይ የሚቃጠል መሆኑ፤

110. በናሙና ተመርጠው በታዩትና በተከለሱት ማስረጃዎች በተለያዩ የአበባ እርሻ ድርጅቶች 662.8 ሄክታር መሬት ያልለማ ሲሆን፤ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ጠንካራ የክትትል ስርዓት በመዘርጋት ለአልሚዎች (ኩባንያዎች) የተሰጣቸውን መሬት በአግባቡ እንዲጠቀሙና የመሬት ብክነትን ለማስወገድ ክትትልና ድጋፍ ያላደረገ መሆኑ፡፡

111. የአበባ አልሚ ባለሀብቶች ፈቃድ ሲያወጡ ጀምሮ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት (ከኢንቨስትመንት ኮሚሽን እንዲሁም ከአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን እና ክልሎች) ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ያልዳበረ መሆኑ፣ በኦዲቱ የታዩ ክፍተቶች ናቸው፡፡

በመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር የመስኖ ልማት አጠቃቀምና አገልገሎት አሰጣጥ እና አፈፃፀምን በተመለከተ፣

112. የመስኖ ፕሮጀክቶቹ ወደ ልማት ከገቡ በኋላ የመስኖ ልማት አፈፃፀማቸውን ለመከታተል የሚያስችሉ ስታንዳርዶችና መመሪያዎች የሌሉ መሆኑ፤ እንዲሁም የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ደንብና መመሪያ ያልተዘጋጀ መሆኑ እና የውሃ አጠቃቀም ስትራቴጂ የሌለ መሆኑ፤

113. የመስኖና ድሬኔጅ መመሪያ፣ መስፈርቶች (Standard) እና የጥገና ኦፕሬሽን መመሪያና ማኑዋሎች እና ለመስኖ ፕሮጀክቶች ለጥገና አገልግሎት የሚውሉ እቃዎች እና ከውጪ ሃገር የሚገቡ የመስኖ ልማት ቴክኖሎጂዎች የጥራት መስፈርት (Standard) የሌለ መሆኑ፤

114. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶችን በመረከብ እያስተዳደረ አለመሆኑ እና ፕሮጀክቶቹ ባለቤት አልባ በመሆናቸው ከኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን ወደ መስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር ባልዞሩበት እና ጥቅም እየሰጡ ባልሆኑበት ሁኔታ ከ320 ሚለዮን ብር በላይ ለግድብና መስኖ ተቋማት አስተዳደር ስራዎች ወጪ የወጣ መሆኑ፤

115. **ተንዳሆ የመስኖ ልማት ፕሮጀክት፡** 1997 ዓ.ም የተጀመረ ሆኖ በሁለት ዓመት ለመገንባት ቢታቀድም ፕሮጀክቱ ከአስር ዓመት በኃላ የተጠናቀቀ እና ብር 4,150,251,145 የፈጀ ሲሆን 60,000 ሄክታር የመስኖ መሬት ለማልማት አቅም ያለው ቢሆንም ከ25-30 ሺህ ሄክታር መሰረተ ልማት ተሰርቶለት 25 ሺህ ሄክታር ሸንኮራ አገዳ ተተክሎ ሥራ የጀመረ ቢሆንም አሁን ላይ አገልግሎት እየሰጠ አለመሆኑ፤

116. **ከሰም የመስኖ ልማት ፕሮጀክት፡** በ2012 እ.ኤ.አ (2005 ዓ.ም) ግንባታ የተጀመረ እና ብር 2,640,812,843.00 የፈጀ ቢሆንም የማልማት አቅሙ 20,000 ሄክታር ሲሆን የመስኖ የመሰረተ ልማት ግንባታ የተካሄደው በ5,000 ሄክታር መሬት ላይ ብቻ መሆኑን እና እስካሁን ያለማው 2,784 ሄክታር መሆኑ፤

117. **የመካከለኛው አዋሽ የመስኖ ልማት ፕሮጀክት፡-** በስድስት ወረዳዎች ከ120 ሺ. ሄክታር በላይ እንዲያለማ ታስቦ የነበረ ቢሆንም 4ቱ ወረዳዎች በ2012 ዓ.ም በጎርፍ የተጎዱ በመሆኑ እስከ አሁን በአሚባራና በሃሩካም 20 ሺ. (16.6 በመቶ) ሄክታር ጥጥ እያለማ ቢሆንም በቀሪዎቹ 4ቱ ወረዳዎች ላይ መልሶ ወደ ልማት ለማስገባት የተሰራ ስራ አለመኖሩ፤

118. **የታችኛው አዋሽ የመስኖ ፕሮጀክቶች** ዋና ካናሎች ተበላሽተው አገልግሎት እየሰጡ ባለመሆኑ 25,152 ሄክታር የማልማት አቅም ቢኖረውም በዱብቲ ወረዳ ብቻ ወደ 4000 ሄክታር አካባቢ (15.9 በመቶ) እየለማ መሆኑ፣

119. **አድአ በቾ የመስኖ ልማት ፕሮጀክት፡-** 5000 ሄክታር ለማልማት በ2002 ዓ.ም 90 (ዘጠና) የከርሰ ምድር ጉድጓዶች ተገንብተው የነበረ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ አስር (10) ጉድጓዶች አገልግሎት የጀመሩ ቢሆንም በትቦ ዝርጋታ ችግር ምክንያት ልማት ጀምረው ያቆሙ ሲሆን ችግሩ ባለመፈታቱ እስከ አሁን አገልግሎት እየሰጡ አለመሆኑ፤ እንዲሁም 80ዎቹ ጉድጓዶች የመስኖ መሰረተ ልማት ስላልተዘጋጀላቸው ልማት ያልጀመሩ መሆኑ፤

120. **አልዌሮ የመስኖ ልማት ፕሮጀክት፡** ፕሮጀክቱ በ1990 እ.ኤ.አ ግንባታው ተጀምሮ በ1994 እ.ኤ.አ የተጠናቀቀ እና ብር 648,686,389.00 የፈጀ ሲሆን ግድቡ ከተጠናቀቀበት ጊዜ ጀመሮ ውሃ የሞላ ቢሆንም የማልማት አቅሙ 10000 ሄክታር ሲሆን ሌላ የማስፋፋት ስራ ቢሰራለት ተጨማሪ 7000 ሄክታር ማልማት የሚችል ሲሆን የመስኖ መሰረተ ልማት ያልተሰራለት በመሆኑ የመስኖ ልማት እያለማ አለመሆኑ፤

121. **የመቂ ዝዋይ 1፡-** የመስኖ ልማት ፕሮጀክት በባለቤትነት የሚከታተለው የሌለውና ጥገና ያልተደረገለት መሆኑ፤ **የመቂ ዝዋይ** 2 የመስኖ ልማት ፕሮጀክት ግንባታዉ ተጠናቅቆ ልማት ሳይጀምር ጥገና የሚያስፈልገው መሆኑና የጥገና ስራው ያልተጀመረ መሆኑ፤

122. **ጎዴ የመስኖ ልማት ፕሮጀክት፡-** እ.ኤ.አ በ1987 ግንባታ ተጀምሮ እ.ኤ.አ በ1998 የተጠናቀቀ እና ብር 393,232,097.00 የፈጀ ሲሆን፤ 27,600 ሄክታር የማልማት አቅም ያለው ቢሆንም ለዋና ካናሉ ቅርብ የሆነው የአካባቢው ማህበረሰብ 2,000 ሄክታር (7.3 በመቶ) ብቻ ልማት እያለማ መሆኑ፤

123. **ርብ የመስኖ ልማት ፕሮጀክት፡** ፕሮጀክቱ በ2002 ዓ.ም ግንባታ የጀመረና 10 ዓመት ያስቆጠረ፣ ብር 3,613,477,436.99 የተመደበለት እና በ6 ዓመት ለማጠናቅ የታቀደ ሲሆን ከታቀደለት በላይ ብር 2,277,203,078.91 እና 6 አመት ተጨማሪ ጊዜ የወሰደ መሆኑ፡፡ ይሁን እና ግድቡ ከተጠናቀቀበት ጊዜ ጀመሮ ውሃ የሞላ ቢሆንም የመስኖ መሰረተ ልማት ያልተሰራለት በመሆኑ አሁንም ድረስ ለመስኖ ልማት አገልግሎት ያልዋለ መሆኑ፤

124. **ኦሞ ኩራዝ የመስኖ ፕሮጀክት** የማልማት አቅሙ 175 ሺህ ሄክታር ሲሆን 25 ሺህ ሄክታር (14 በመቶ) ብቻ ሸንኮራ አገዳ እያለማ መሆኑ፤

125. **ጣና በለስ የመስኖ ፕሮጀክት** የማልማት አቅሙ 50,000 ሄክታር ሲሆን እያለማ ያለው 15,000 ሄክታር (30 በመቶ) ብቻ መሆኑ፤

126. **የቆቦ-ጊራና ሸለቆ መስኖ ልማት ፕሮጀክት፡** ፕሮጀክቱ እስከ ምንጃር ሸንኮራ ያለውን ሰፊ መሬት እንዲያለማ ታስቦ ከ20 አመት በፊት የተቋቋመ ቢሆንም በሙሉ አቅሙ የመስኖ ልማት አገልግሎት እየሰጠ አለመሆኑ፤

127. የመስኖ ውሃ ቁጠባን ለማሳደግ የውሃ፣ የጥገናና ኦፕሬሽን አገልግሎት ክፍያ የአሰራር ስርዓት የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን በስራ አመራር ቦርድ መመሪያውን አጽድቆ አልሚዎች እንዲከፍሉ ጠይቆ ፍቃደኛ እንዳልሆኑ፤ ለቀድሞው የውሃ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር ጥያቄ በደበዳቤ ጥያቄ ቢያቀረብም ምንም ምላሽ ያልተሰጠው መሆኑ፤ እስከአሁን ድረስ ስርዓቱ ባለመዘርጋቱ የመስኖ ውሃ አቅርቦት አገልግሎት ክፍያ ከ3.25 ቢሊዮን ብር በላይ ታሪፉ ያልተሰበሰበ መሆኑ፣ ይህን ችግር በሌላ ኦዲት ያመላከትነው ቢሆንም እስካሁንም እልባት ያላገኘ መሆኑ ታወቋል፡፡

<u>በግብርና ሚኒስቴር የስርዓተ ጾታ አካታችነት አፈጻጸም ውጤታማነትን በተመለከተ፣</u>

128. የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/2005 የሴቶችን የመሬት ባለ መብትነትና ተጠቃሚነት ባለማካተቱ አዲስ ረቂቅ አዋጅ በ 2014 ዓ.ም የተዘጋጀ ቢሆንም ረቂቅ አዋጁ ይህ ኦዲት አስከ ተጠናቀቀበት ህዳር 2015 ዓ.ም ድረስ አለመጽደቁ፣

129. በኦዲት ቡድኑ በናሙና ተመርጠው በታዩት አራት ክልሎች(አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ሶማሌ እና ሀረሪ) እና በስራቸው ባሉ ዞኖች ወረዳዎች የሴቶችን የእርሻ ምርት፤ የጓሮ አትክልቶች፤ ፍራፍሬዎች እና የእንስሳት ሀብት እንዲሁም ሌሎች ንብረቶች ከወንድ የትዳር አጋራቸው እኩል የማስተዳደር እና የመጠቀም ልምድ እንዲዳብር አለመሰራቱ፣

130. በሚኒስቴር መ/ቤቱ እየተተገበረ በሚገኘው በምርታማ ሴፍትኔት ፕሮግራም ፌዝ 4 እና 5 ፕሮጀክት በኩል ፕሮጀክቱ ከተጀመረበት ከ2011 ዓ.ም ይህ ኦዲት እስከ ተጠናቀቀበት ህዳር 2015 ዓ.ም ድረስ ፕሮጀክቱ በሚተገበርባቸው አራት ክልሎች 574 በመጀመሪያ ምእራፍ እና 1,164 በማስፍፊያ ፕሮግራም የስርአተ ጾታ ሞዴል ቤተሰቦች እንዲመረቁ በማድረግ ወንዶች የሴቶቹን የስራ ጫና እንዲያግዙ እና ሴቶች በቀጥታ ገቢ የሚያስገኙ ስራዎች ላይ እንዲያተኩሩ እና የሚገኘውን ገቢ ማስተደደር እና መጠቀም እንዲችሉ ቤተሰባዊ መተጋገዝ መረዳዳት እና መተማመን ላይ እንዲደርሱ የማገዝ ስራዎች ቢኖሩም ከላይ የተገለጸው ቁጥር ከአጠቃላይ ማህበረሰቡ አንጻር በጣም ዝቅተኛ መሆኑ፣

131. የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የ10 አመት መሪ እቅድ፣ የ2011 ዓ.ም እቅድ፣ የ2012 ዓ.ም እቅድ እና የ2013 ዓ.ም እቅድ በጾታ በተከፋፈለ መረጃ ወይም የሴት እና የወንድ አርሶ/አርብቶ አደሮችን በቁጥር በሚያሳይ መልኩ አለመታቀዱ፤

132. ከፌዴራል ህብረት ስራ ኮሚሽን በተሰበሰበ መረጃ መሰረት በሃገር አቀፍ ደረጃ 25,507,304 የህብረት ስራ አባላት ያሉ ሲሆን ከዚህም ውስጥ የሴቶች ድርሻ 8,017,944(31.4)% እንደሆነ ታውቋል፡፡

133. በግብርና ስራ የሚተዳደሩ እማወራዎች ምርታማነታቸው ከአባወራዎች የቀነሰ ቢሆንም ሴቶችን ቅድሚያ በመስጠት ድጋፍ የሚደረግበት ስርአት ወይም የህግ ማአቀፍ የሌለ መሆኑ፤ ታውቋል፡፡

በጤና ሚኒስቴር የዘላቂ ልማት ግብ 3 በጤናው ዘርፍ ላይ የስርዓተ-ጾታ እኩልነትና ተጠቃሚነት አፈጻጸምን በተመለከተ፣

134. በጤና ተቋማት (የግልና የመንግሥት) በወሊድ ወቅት የእናቶች ሞት በባለሙያ/ በሀኪም ስህተት (Human Error)፣ ቸልተኝነት እና የስነ-ምግባር ግድፈት (Medical Negligence) ምክንያት ሲሆን ጉዳዩን ለማስተካከልና ተጠያቂነትን ለማስፈን የሚያስችል በሁሉም ጤና ተቋማት ውስጥ ተግባራዊ ሊሆን የሚችል የተዘጋጀ የህክምና ስነ-ምግባር ደንብ/መመሪያ (Medical Code of ethics and conduct Manual) በኦዲቱ ወቅት ተጠይቆ ያልቀረበ መሆኑ፣

135. በሚኒስቴር መ/ቤቱ እ.አ.አ ከ2016-2020 በተዘጋጀው የጤና ዘርፍ ዕቅድ መሠረት የቅድመ ወሊድ ክትትል 4 ጊዜና ከዛ በላይ የሚያገኙ ነፍሰ ጡር እናቶች ሽፋን ከ68 በመቶ ወደ 95 በመቶ ማሳደግ እንዲሁም እ.አ.አ. ከ2021-2025 በተዘጋጀው ሁለተኛ የጤና ዘርፍ ዕቅድ የቅድመ ወሊድ ክትትል 4 ጊዜና ከዛ በላይ የሚያገኙ ነፍሰ ጡር እናቶች ሽፋን ከ43 በመቶ ወደ 81 በመቶ ማሳደግ በሚል የታቀደ ሲሆን የሁለቱ ጊዜያት ዕቅድ ሲነጻጸር የመጀመሪያው እቅድ 68 በመቶ የነበረው መነሻ ዕቅድ የሁለተኛው ጊዜ ላይ ወደ 43 በመቶ የወረደ መሆኑ ታይቷል፡፡

በገቢዎች ሚ/ር የታክስ መረጃ አስተዳደር ሥርዓት አፈጻጸም በተመለከተ

136. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የዘረጋው የታክስ መረጃ አስተዳደር ሥርዓት ሁሉንም የታክስ መረጃ ምንጮች ባማከለ መልኩ በጥራት የማይሰበስብ፣ የማይደራጅ እንዲሁም ወቅታዊ የማይደረግ መሆኑ፣

137. የታክስ አስዳደር ስርአት ላይ የተመዘገቡ የግዥና የሽያጭ መረጃዎች ሲስተም ውስጥ ያለውና በሰነድ ላይ ያለው የማይጣጣም እና መረጃው ያልጠራ መሆኑ፣

138. የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አቅርቦት ባለመኖሩ የሽያጭ መመዝገቢያ ማሽን የማይጠቀሙ ግብር ከፋዮች መኖራቸው፣በአገሪቱ የሚሰበሰበው ግብር ላይ ተጽእኖ የሚያሳድር መሆኑ፣

139. የሽያጭ መመዝገቢያ የማይጠቀሙ ግብር ከፋዮች የግዥና የሽያጭ መረጃቸውን በምን መልኩ ወደ ታክስ እንደሚያስገቡ የተዘረጋ የአሰራር ስርዓት አለመኖሩ፣

140. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የግብር ከፋዮች የሚጠቀሙበት የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ሲስተም ላይ የተመዘገቡና ያልተመዘገቡ፣ የሚሰሩ የማይሰሩ እና መረጃ ቋት (database server) ላይ መረጃ የሚልኩና የማይልኩትን በማዕከል ደረጃ እንዲታወቅ

ያለደረገ መሆኑ፣ በክልል ደረጃ ምን ያህል የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ እንዳለ፣ ምን ያህሉ የሚሰራ እና የማይሰራ እንደሆነ የሚታወቅበት ሁኔታ አለመኖሩ፣ በሀገሪቱ ውስጥ ያሉት የሽያጭ መመዝገቢያ ማሽኖች GPS ያልተገጠመላቸው መሆኑ፣

141. የሽያጭ አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 46/1999 አንቀፅ 9(7) መሰረት የማሽን አቅራቢዎች በ48 ሰዓት የጥገና አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑ፣

142. በሚኒስቴሩ የተደራጁ የተለያዩ የመረጃ ቋቶች (የመንግስት ታክስ አስተዳደር ስርዓት (SIGTAS)፣ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ (CRM)፣ የጉምሩክ ስነስርዓት ለገቢ ዕቃዎችም ሆነ ለወጪ ዕቃዎች የሚከናወንበት (ኢ.ሲ.ኤም. ኤስ./eCMS) (electronic custom administration system) በተያዘው መረጃ መካከል እርስ በእርሳቸው የሚናበቡበት (Interface) የአሰራር ስርዓት ባለመዘርጋቱ መረጃዎቹ እረስ በርስ የማይናበቡ መሆኑ የሚሉት ዋና ዋና ግኝቶች ናቸው፡፡

<u>**የትምህርት ሚኒስቴር የመረጃ ማዕከል ግንባታና የመረጃ አስተዳደር ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ**</u>

143. ትምህርት ሚኒስቴር በአገር ደረጃ የትምህርት ተቋማትን መረጃዎች ሙሉ በሙሉ አደራጅቶ በመያዝ እያስተዳደረ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለተማሪዎች የመረጃ ስርዓት (Student Information System) የሚጠቀሙባቸው ሲስተሞች ወጥ ባለመሆናቸው ወደ አንድ የመረጃ ሥርዓት ለማምጣት አመቺ አለመሆኑ፤

144. ለፕሮጀክቶች የቅድመ አዋጭነት እና የአዋጭነት ጥናት ያልተጠና በመሆኑ ፕሮጀክቶቹ ለተቋማቱ ያላቸውን ጠቀሜታም ሆነ ፕሮጀክቶቹን ተከትለው ለሚመጡ የጎንዮሽ ችግር የመፍትሔ አቅጣጫ ለማስቀመጥ አስቸጋሪ መሆኑ፤

145. በተጨማሪም ኢተርኔት ምዕራፍ-2 ፕሮጀክትን ለመስራት እንደ አንድ ብቸኛ ተወዳዳሪ ተቆጥረው ሥራዎችን ለወሰዱ ድርጅቶች ያለህጋዊ ውል እና አማካሪ የተሰጠ በመሆኑ ስራዎች በሚዘገዩበት ጊዜ ተጠያቂ ማድረግ አለመቻሉ፤

146. በትምህርት ሚኒስቴር እየተሰሩ ካሉ በናሙና ከታዩ አራት ፕሮጀክቶች ውስጥ ኢተርኔት ምዕራፍ-2 (Entrenet Phase II) ፕሮጀክት መቼ ተጀምሮ መቼ እንደሚጠናቀቅ የጊዜ ገደብ ያልተቀመጠለት ሲሆን ሦስቱ ፕሮጀክቶች ደግሞ በውል ስምምነቱ ላይ በተቀመጠላቸው ጊዜ ሳይጠናቀቁ ከ 1 ዓመት እስከ 5 ዓመት በመዘግየት ከፕሮጀክቶቹ የሚጠበቀውን አገልግሎት እየሰጡ አለመሆናቸው፤

147. በተለይም የሞጁላር ዳታ ማዕከል ፕሮጀክት ከተቋረጠ ከሁለት አመት በላይ ቢሆነውም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ የማስተካከያ እርምጃ መወሰዱን የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤

148. በኢተርኔት ምዕራፍ -1(Entrenet Phase I) ፕሮጀክት 36 የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ከፍተኛ ፍጥነት ባለው ኔትወርክ እርስ በራሳቸው እና ከአለም አቀፍ የትምህርትና ምርምር ተቋማት ጋር በኔትወርክ ለማስተሳሰር የተከናውነው ፕሮጀክት ተጠናቋል ቢባልም ዩኒቨርሲቲዎቹ ከፕሮጀክቱ ማግኘት ያለባቸውን አገልግሎቶች እያገኙ አለመሆኑ፤ ለዚህ ፕሮጀክት ስራ የተላኩ ዕቃዎችም ከ 6 ዓመት በላይ ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆናቸው፤

149. እንዲሁም በኢተርኔት ምዕራፍ 2 ፕሮጀክት ዩኒቨርስቲዎች የተሟላና አለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ አስተማማኝ የአይሲቲ መሰረተ ልማትና የካምፓስ ኔትወርክ እንዲኖራቸው በማድረግ በመጀመሪያው ምዕራፍ ያልተካተቱ ተቋማትን በማካተት ለትምህርት አገልግሎት ብቻ የሚውል(Private Educational Cloud) አገልግሎት እንዲያገኙ ለማስቻል ስራዎች የተጀመሩ ቢሆንም የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት አቀናጅቶና ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ መስራት ባለመቻሉ የተፈለገውን አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ስራ ያልተሰራ መሆኑ፤

150. ለኢተርኔት ምዕራፍ-2 ፕሮጀክት ሥራ የኮንትራት ውል ስምምነት ሳይፈፀም ብር 109,000,000.00 የተከፈለ መሆኑ፤ ይሁን እና በናሙና በታዩ ዩኒቨርሲቲዎች ላይ ሥራው ያልተጀመረ መሆኑ፤

151. ትምህርት ሚኒስቴር የምርምር ጥናት ኩረጃን መቀነስ የሚያስችል በቴክኖሎጂ የታገዘ አሰራርን ለመዘርጋት ሃገራዊ የመረጃ ቋት (National Academic Digital Repository of Ethiopia (NADRE)) ቢያቋቁምም በዩኒቨርሲቲዎችና ካምፓሶች የተሰሩ የምርምር ስራዎች ወደ ሃገራዊ የመረጃ ቋት ገብተው ያልተያዙና የምርምር ጥናት ኩረጃን መቀነስ ያልተቻለ መሆኑ፤

152. በ300 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና በ10 ዩኒቨርሲቲዎች ላይ ተግባራዊ ለማድረግ የተዘረጋው የክላውድ መሰረተ ልማት ፕሮጀክት እና የሞጁላር ዳታ ማዕከል የመሰረተ ልማት ዝርጋታ ፕሮጀክት የመጨረሻ የተቀባይነት ፍተሻዎች (final Acceptance tests) በማከናወን የመጨረሻ ክፍያ እንዲከፈል ያልተደረገ መሆኑ፤

153. በናሙና በታዩ ት/ቤቶች የተተከሉትን ሰርቨሮች፣የኮምፒውተር ቤተ ሙከራዎች እና የተዘረጋውን ኔትወርክ በአግባቡ እንዲያስተዳድሩ የሚያስችል ቴክኒካልና የተግባር (Operational) ሥልጠናዎችን የሰለጠኑ ባለሙያዎች ያልተመደቡ መሆኑ፣

<u>በሀዋሳ ዩኒቨርስቲ የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ እና የውስጥ ገቢ ማመንጫ (ሪሶርስ ሞባላይዜሽን) የስራ አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ጤታማ መሆኑን በተመለከተ</u>

154. የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች የሚተዳደሩበት መመሪያ ቁጥር 04/2012 አንቀጽ 7 እና አንቀጽ 8 (1) እና (2) መሰረት የኢንተርፕራይዙ መቋቋሚያ ካፒታል በቦርድ ሊወሰን እና ከተወሰነበት ጊዜ አንስቶ በአምስት አመት ውስጥ ተከፍሎ መጠናቀቅ እንዳለበት እና የካፒታል ጣራ ከተሟላ ደግሞ የትርፉን 80 ከመቶ ለዩኒቨርሲቲ ተልዕኮ እና ዓላማ ማስፈጸሚያ ሊዉል ይገባል ይላል፡፡

155. በዚሁ መሰረትም ተግባራዊ ማድረጉን ለማረጋጋጥ ኦዲት ሲደረግ በ2012 ዓ.ም ብር1,913,716.48 እና በ2013 ዓ.ም ብር 710,045.74 ካገኘው ትርፍ ላይ 80 ፐርሰንቱን ኢንተርፕይዙ ለዩኒቨርሲቲዉ ፈሰስ ያላደረገ መሆኑ፣

156. በተጨማሪም በመቋቋሚያ ደንባቸው ላይ በዋና ኦዲተር ወይም እሱ በሰየማቸዉ ኦዲት እንደሚደረግ ቢጠቅስም ዩኒቨርሲቲው በሰየማቸው ኦዲተሮች ኦዲት የሚያስደርጉ መሆኑ፣

157. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 456/2012 አንቀጽ 6 (2) የዩኒቨርሲቲ ቦርድ የዩኒቨርሲቲ መምህራንና ተመራማሪዎች በገቢ ማስገኛ ድርጅቱ ስለሚኖራቸው ተሳትፎና ስራን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ተያያዥ መመሪያዎችን እንደሚያጸድቅ ሲደነግግ እንዲሁም የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገቢ ማስገኛ ድርጅቶች የሚተዳሩበትን ሥርዓት ለመወሰን በወጣ መመሪያ ቁጥር 4/2012 በዩኒቨርሲቲ ተቀጣሪዎች በገቢ ማስገኛ ድርጅቱ ተቀጣሪ ሆነው ማገልገል እንደማይችሉ ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ፡-

158. ኢንተርፕራዙ የዩኒቨርስቲን መምህራኖችና ተመራማሪዎች እንዴት እንደሚጠቀምባቸው መመሪያ/መስፈርት ሳያወጣና በቦርድ ሳያጸድቅ ማለትም (የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የውሃና ውሃ ነክ መሃንዲሶች አጠቃላይ የውሃ ሀብት ልማት አማካሪ ማህበር እና የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት አጠቃላይ የሲቪልና ተዛማጅ ስራዎች ዲዛይን፣ ሱፐርቪዢንና አማካሪ ማህበር) ጋር ዉል በመፈራረም በማማከር አገልግሎት የሚጠቀም መሆኑን ነገር ግን ማህበራቱ ህጋዊ ሰውነት ያላቸው እና በህግ ሥልጣን በተሠጠ አካል በማህበርነት ስለመደራጀታቸ ማስረጃ ተጠይቆ ያልቀረበ እና የንግድ ፈቃድ የሌላቸው እና የኢንተርፕራይዙን ንግድ ፈቃድ የሚጠቀሙ መሆኑ፤

159. የክፍያው ሁኔታም ከሚገኘው ትርፍ የዩኒቨርስቲው መምህራን 85% የትርፍ ድርሻ ሲኖራቸው ኢንተርፕራይዙ 15% ብቻ የትርፍ ድርሻ እንዲኖረው የተስማማ መሆኑ፤

160. በዚሁ መሰረትም ኢንተርፕራይዙ ከተቋቋመ ጊዜ ጀምሮ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ከብር 59,828,688.42 በላይ ክፍያ የፈጸመላቸው መሆኑ፤

161. ኢንተርፕራይዙ የመንግስት ሰራተኞች የቀን ውሎ አበል መመሪያን የሚጠቀም መሆኑን ባዘጋጀ የሰዉ ሀብት አስተዳደር መመሪያ ላይ ያስቀመጠ ሲሆን ነገር ግን በመስክ አገልግሎት ላይ ለሚሠማሩ ባለሙያዎችና የአስተዳደር ሠራተኞች እንዲሁም ሌሎች ተሳታፊዎች ከተቀመጠው መመሪያ ዉጭ እና ቦርድ ባላጸደቀው የአበል ተመን የሚከፍሉ መሆኑ፣

162. ኢንተርፕራይዙ የዩኒቨርስቲው የስራ አመራር ቦርድ ባላጸደቀበት ሁኔታ ብር 1,015,073.85 የቦነስ ክፍያ በማለት የከፈለ መሆኑ፣

163. ለኢንርፕራይዙ የተመደቡት ቦርዶች ከ2012 ጀምሮ ተሰብስበው ስለማያውቁ የቦርድ ውሳኔ የሚያስፈልጋቸው ከላይ የተገለጹትን እና በዋናው ሪፖርት የተጠቀሱትን ስራዎች በቦርድ ሳይጸድቁ እየተፈጸሙ መሆኑ በኢንተርፕራይዙ ላይ የታዩት ክፍተቶች ዋነኛ መንስኤ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለመረዳት ችለናል፡፡

<u>በጤና ሚኒስቴር የፌዴራል ሆስፒታሎች የሕክምና መሣሪያዎች አገልግሎት አሠጣጥ አፈፃፀምን በተመለከተ</u>

164. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በህክምና መሣሪያዎች አገልግሎት አሰጣጥ ተደራሽ መሆኑን እና ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን የተዘረጋ የአሰራር ስርዓት መኖሩን እና የተዘረጋው የአሰራር ስርዓትም ቀልጣፋ እና ዉጤታማ እንዲሁም የመረጃ ቅብብሎሹ ዘመናዊ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ክፍተቶች በኦዲቱ ታይተዋል፡፡

165. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሆስፒታሎችን የህክምና መሳሪያ ፍላጎት በመጠየቅ እና በቅድሚያ በአመታዊ የግዢ እቅድ ውስጥ በማካተት ግዥ የማያከናውን መሆኑ፣

166. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለጤና ተቋማት (ለሆስፒታሎች) የተላከላቸው የህክምና መሳሪያዎች በትክክል ስለመድረሳቸው ክትትል የሚያደርግበት ሥርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፣

167. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ለማድረግ የሚረዳ የረጅም ጊዜ ዕቅድ ቢያዘጋጅም የሚደረስበት ኢላማና የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣

168. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፌዴራል ሆስፒታሎች በእርዳታ የሚገቡ የህክምና መሳሪያዎች ርክክብ ከመደረጉ በፊት በህክምና መሳሪያዎች አስተዳደር ኮሚቴ ወይም በሆስፒታሎች ማኔጅመንት እየተረጋገጠ ርክክብ የሚደረግ ስለመሆኑ የሚከታተልበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣

169. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሆስፒታሎች በስራ ላይ ያሉ ህክምና መሳሪያዎች መደበኛ የፍተሻ ፕሮግራም ተዘጋጅቶ የሙያ የደህንነት ፍተሻ (inspection and testing) እያስደረጉ ስለመሆኑ ክትትል የሚያደርግበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣

170. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሆስፒታሎች የሚገኙ የህክምና መሳሪያዎች ለመሣሪያዎቹ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ትክክለኛነታቸውን በየጊዜው ለማረጋገጥ የመለካት (Calibration) መደረጋቸዉን የሚያረጋግጠብት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣

171. የህክምና መሳሪያዎች ከአንዱ የመንግሰት ተቋም እጥረት ወይም ብልሽት በሚያጋጥምበት ግዜ የዜጎችን እንግልት እና ችግር ለማቃለል ከሌላዉ የመንግስት የህክምና ተቋም በጋራ በመረዳዳት ለመስራት የሚያስችል የተዘረጋ የአሰራር ስርዓት የሌለ መሆኑ የሚሉት ዋና ዋና ግኝቶች ናቸው፡፡

<u>የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር በስምጥ ሸለቆ ውስጥ ከፍተኛ መጠን ካለው (የበዛ) ፍሎራይድ የነፃ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት አፈፃፀምን በተመለከተ፣</u>

172. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በስምጥ ሸለቆ አካባቢ ላሉ ነዋሪዎች የሚቀርበው የመጠጥ ውሃ ከፍተኛ መጠን ካለው የፍሎራይድ ንጥረ ነገር የቀነሰ እንዲሆን ለማድረግ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን እንዲሁም የፍሎራይድ ፕሮጀክትን የሚያሰሩ ከተሞችና ወረዳዎች ለፕሮጄክቶቹ በተያዘው በጀት፣ ጊዜ፣ ጥራትና ደረጃ መሰረት ፕሮጀክቱን ማሰራታቸውን እና ለህብረተሰቡ የሚቀርበው ከፍተኛ መጠን ካለው የፍሎራይድ መጠን የታከመ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ዘላቂነት ያለው መሆኑን እና በስምጥ ሸለቆ ውስጥ የፍሎረሲስ መከላከል ፕሮጀክቶች ትግበራ ላይ የሚመለከታቸው አካላት የሚያደርጉትን ክትትልና ቁጥጥርን በተመለከተ የተደረገ ኦዲት ሲሆን በኦዲቱ ወቅትም የተገኙ ክፍተቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

173. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ በሰምጥ ሸለቆ ውስጥ ከሚገኙ በአሮሚያ ክልል በሁለት ዞን በሶስት ወረዳዎች፣ በደቡብ ክልል በሶሰት ዞን እና በሶስት ወረዳዎች ለፍሎራይድ ተጋላጭ አካባቢዎች የተጣራ ንፁህ የመጠጥ ውሃ ተደራሽ ማድረግ አለመቻሉና በአስገዳጅ የኢትዮጵያ ንጹህ የመጠጥ ውሃ ደረጃ ከፍተኛው 1.5 ሚ .ግራም በሊትር ቢሆንም በነዚህ ወረዳዎች ግን በሊትር ከ9.3 እስከ 18.3 ሚሊ ግራም የተገኘባቸው መሆኑ፣

174. በስምጥ ሸለቆ ውስጥ የሚገኙ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል 35 ወረዳዎች፣ በኦሮሚያ ክልል 44 ወረዳዎች፣ በአፋር ክልል 10 ወረዳዎች በድምሩ 89 ወረዳዎች ሲሆኑ ከዚህ ውስጥ 27 ወረዳዎች (ኦሮሚያ 13፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል 7፣ በአፋር ክልል 7 ወረዳዎች) በከፍተኛ ፍሎራይድ የተጠቁ መሆናቸው፣

175. ከፍተኛ የፍሎራይድ ስርጭት ካለባቸው 89 ወረዳዎች መካከል የፍሎራይድ ማጣሪያ ቴክኖሎጂዎች የተገነቡት በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በ3 ወረዳዎች ባሉ 9 ቀበሌዎች ለ29,899 የህብረተሰብ ክፍሎች በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል በ5 ወረዳዎች ባሉ 8 ቀበሌዎች 112,704፣ በሁለቱ ክልሎች 142,603 ኗሪዎች ብቻ የተገነባ መሆኑ፣

176. በሚኒስቴር መ/ቤቱ በ2014 ዓ.ም በናሙና ከታዩት ፕሮጀክቶች መካከል 30 የፍሎራይድ ማጣሪያ ቴክኖሎጂዎች መካከል 22 (73%ቱ) በተለያዩ ምክንያቶች የማይሰሩ መሆኑ እና 8 (27% ቱ) ብቻ የሚሰሩ መሆኑ፣

177. በናሙና በታዩት ወረዳዎች ከፍሎራይድ ያልተጣራ ውሃ እንኳን ለማግኘት በአማካይ ከ7 ኪ.ሜ በላይ ህብረተሰቡ የሚጓዝ መሆኑ፣

178. በ10 ዓመቱ የሀገሪቱ የልማት ዕቅድ ላይ ከ3.5 ሚሊዮን ለፍሎራይድ ተጋላጭ የሆነዉን የህብረተሰብ ክፍል ቁጥሩን ወደ ዜሮ ለማዉረድ የታቀደ ሲሆን ሚ/ር መ/ቤቱ የዘርፉ እቀድ ሲያዘጋጅ ግን ከ3.5 ሚሊዬን ወደ 2.5 ሚሊዬን ለማዉረድ ነው እቀድ የተያዘው፤ ይሁን እንጂ የሀገሪቱ እቅድ እና የሚ/ር መ/ቤቱ እቅድ እንደማይጣጣም በኦዲት ወቅት ለማየት ተችሏል፡፡

<u>**በኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር በአዘዞ-ጎንደር እና ጎንጂ-ቆለላ እና በኮከብ መስክ - አለም ከተማ፣ አለምከተማ - ደጎሎ እና ዶጎሎ - ከለላ የመንገድ ማሻሻያ ግንባታ ፕሮጀክቶች አፈጻጸምን በተመለከተ**</u>

179. **የአዘዞ-ጎንደር እና የጎንጂ-ቆለላ መንገድ ፕሮጀክትን** ለመገንባት አስተዳደር መስሪያ ቤቱ ከመወሰኑ በፊት የቅድመ አዋጭነት ጥናት ያላስጠና እና የፕሮጀክቶቹን መሰረታዊ ይዘቶች ማለትም የፋይናንስ፣ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ አዋጭነትና የቴክኒክ አግባብነት እና አካባቢያዊ ተፅዕኖ ጥናት ሳያጠና ወደ መንገድ ግንባታ ስራ የገባ መሆኑ፣

180. አስተዳደር መ/ቤቱ የአዘዞ-ጎንደር እና ጎንጂ-ቆለላ መንገድ ፕሮጀክት ከ80 በመቶ በላይ ለሚሆኑት የልማት ተነሽዎች ካሳ ወይም ምትክ ቦታ ሳይሰጣቸው ከቦታቸው እንዲነሱ የተደገረ መሆኑ፣

181. አስተዳደር መ/ቤቱ በየጊዜው በመስክ በሚያደርጋቸው የሥራ ጉብኝቶች እያንዳንዱን የግንባታ ሂደት አፈጻጸም ውጤት እና የሚስተዋሉ ችግሮችን ትኩረት ሰጥቶ መስራት ባለመቻሉ የመንገድ ፕሮጀክቶቹ ዘርፈ ብዙ ችግሮች የገጠማቸው እና ከ1 ዓመት እስከ 3 ዓመት የተጓተቱ መሆኑ፣

182. አስተዳደር መ/ቤቱ የሥራ ተቋራጮች ቀድሞ የተረከቡትን ሥራ በወቅቱ ሳያጠናቅቁ ተደጋጋሚ ሌላ ተጨማሪ ሥራ እንዳይሰጣቸው ክትትል ባለማድረጉ፤ ከ 5 በላይ ሌሎች የመንገድ ስራ ፕሮጀክቶችን የያዙ ተቋራጮች መኖራቸው፣

183. የአዘዞ-ጎንደር መንገድ ፕሮጀክት ሥራ ተቋራጩ ዋነኛ ሥራውን ለመጀመር 10 ወራት ያህል የዘገየ በመሆኑ ያለሥራ የቆየበትን የካሳ ክፍያ **9 ሚሊዮን ብር** በፍርድ ቤት አስወስኖ የተከፈለው መሆኑ፣

184. የአዘዞ-ጎንደር መንገድ ስራ ተቋራጭ (ራማ ኮንስትራክሽን) ለመንገድ ግንባታ ሥራ ወደ መስክ /ሳይት/ ያሰማራቸው የግንባታ ማሽነሪዎች፣ መሳሪያዎች እና ዕቃዎች የመንገድ ግንባታውን ለማከናወን በቂ እንዳልሆኑ እና አብዛኛውን በኪራይ የሚቀርብ ከመሆኑ የተነሳ ተቋራጩ በወቅቱ የማሽን ኪራይ ክፍያ ስለማይከፍል በተደጋጋሚ ስራ የሚያቆሙና ስራ ትተው ከሳይት የሚወጡበት ሁኔታ መኖሩ፣

185. አስተዳደር መ/ቤቱ የአዘዞ-ጎንደር እና የጎንጂ-ቆለላ የመንገድ ፕሮጀክቶች ላይ ጨረታ አሸንፈው የገቡ ተቋራጮች በጨረታ ሂደት ወቅት ባሳወቁዋቸው ቁልፍ የሰው ኃይል እያሰሩ እና እያስመሩ አለመሆኑን እና ለውጥ በተከሰተ ወቅት ለአማካሪ መሐንዲሱ እንደማያሳውቁ እንዲሁም አዘዞ-ጎንደር መንገድ ፕሮጀክት ላይ ከነሐሴ ወር 2014 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ህዳር 2015 ዓ.ም ድረስ ማቴሪያል መሃንዲስና ፕሮጀክት ማናጀር ኮንትራክተሩ ያልቀጠረ መሆኑ፣

186. የአዘዞ-ጎንደር መንገድ ፕሮጀክት ተቋራጭ እስከ 2014 በጀት ዓመት አጠቃላይ የፕሮጀክቱ አፈጻጸም መጠናቀቅ ያለበት ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ግዜ ድረስ ያለዉ አፈጻጸም 40.55 በመቶ ብቻ በመሆኑ የጊዜ መዘግየት ቅጣት በአስተዳደር መ/ቤቱ ተፈጻሚ አለመሆኑ፣

187. **የአለም ከተማ ደጎሎ መንገድ ስራ ፕሮጀክት ግንባታ፡-** በአዋጭነት ጥናት እና በኮንትራት ውል መሰረት ለማጠናቀቅ የሚያስፈልገውን ሶስት አመት እና በጀት ደግሞ ብር 1,280,770,840.15 ተይዞለታል፡፡ ከዚህ ዉስጥ ብር 908,539,868.60 ወይም የበጀቱን 49.99% የተጠቀመ ቢሆንም እንደገና በተጨማሪ ለዋጋ ማስተካካያ ብር 199,061,085.52 ተከፍሎት የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቱ ስድስት አመት የሆነው እና አፈጻጸሙም 49% መሆኑ ያዋጭነት ጥናቱ እና የኮንትራት ዉሉ ትክክለኛ ግዜውን ያላመለከተ መሆኑ በኦዲቱ ታይቷዋል፡፡

188. የደጎሎ ከላላ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት በተገባው የኮንትራት ውል መሰረት በታቀደው የጊዜ ሰሌዳ ያልተጠናቀቀ መሆኑ እና ለሦስት ጊዜ የጊዜ ይራዘም ጥያቄ ተቋራጩ የጠየቀ ሲሆን አስተዳደር መ/ቤቱ በአጠቃላይ 1,112 ቀናቶች እንዲራዘም የፈቀደ ቢሆንም የግንባታው ሥራ ያላለቀ መሆኑ፣

<u>የኢትዮጵያ ግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን፤ የግብርና ግብአቶች (ምርጥ ዘር፣ አግሮ ኬሚካሎችና የእርሻ መሳሪያዎች) አቅርቦት፤ሥርጭት እና የብድር አመላለስ በተመለከ</u>

189. ኮርፖሬሽኑ በራሱ እርሻ ልማት ላይ ለሚያመርተው ምርት በዝናብ ላይ ብቻ ጥገኛ ሆኖ በመስራቱ በሚፈለገው መጠን የምርጥ ዘር ምርት ማቅረብ ያልቻለ ሲሆን በዝናብ መብዛትና ማነስ ምክንያት በየዓመቱ ለኪሳራ ተጋላጭ መሆኑ፤

190. ኮርፖሬሽኑ በስትራቴጂክ እቅዱ መሰረት የተለያየ አይነት ያላቸው የጓሮ አትክልት ዘሮችን ለሽያጭ ለማቅረብ በ2013 በጀት ዓመት በብር 45,464,000 እንዲሁም በ2014 በጀት ዓመት በብር 50,010,000 ዋጋ ያለው አትክልት ለማቅረብ በእቀድ ቢይዝም በ2013 እና በ2014 ዓ.ም ማቅረብ ያልቻለ መሆኑ፣

191. የኮርፖሬሽኑ የእርሻ መሳሪያዎች አቅርቦትና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ዘርፍ ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር አገልግሎቶችን ለመሸጥና ለመግዛት ከደንበኞች ጋር በገባው ውል መሰረት በወቅቱ ሊሰበስብ የሚገባ ቢሆንም ከ5-10 ዓመት በላይ ያልተሰበሰቡ ሂሳቦች በአጠቃላይ ብር 17,343,870,979.55 መኖሩ፣

192. የግብርና ሜካናይዜሽንና ኢንጅነሪንግ ዘርፍ ከሚሰጣቸው የሜካናይዜሽን አገልግሎት ስራዎች በ2013 በጀት ዓመት ብር 205,939,000 ገቢ ለማስገባት በእቅድ የተያዘ ሲሆን ክንውኑ ብር 74,908,000 በመቶኛ 36 ብቻ መሆኑ፤

193. በአሰላ ቅርንጫፍ በተለያዩ ዓመታት ተመርተው እና ከውጭ ተገዝተው ለዘር ሳይውሉ የቀሩና በመጋዘን ውስጥ ከ20 ዓመታት በላይ ያስቆጠሩ በኬሚካል የተነከሩ ምስር እና ብቅለታቸው ከመስፈርት በታች የሆኑ የእህል ዘሮች ግምታቸው ከብር 4,765,603.11 በላይ በኮርፖሬሽኑ ሀብት ላይ ተመዝግበው የሚታዩ መሆኑ፣

194. ኮርፖሬሽኑ በግዥ ሰነድ ቁጥር 15542 እና 15544 ከውጪ የገዛቸውን እቃዎች ጉምሩክ ባስቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ዕቃዎቹን ባለማንሳቱ 20% ቅጣት ብር 3,133,395.5 እንዲከፍል የተደረገ መሆኑ፤

195. በ2013/2014 የሰብል ዘመን የአፈር ማዳበሪያ ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ በመጨመሩ ምክንያት መንግስት ለሀገር ውስጥ ትራንስፖርት የሚሆን ብር 4,371,061,624 ቢሊዮን ድጎማ ያደረገ በመሆኑ ገንዘብ ሚኒስቴር ለኮርፖሬሽኑ 2 ቢሊዮን ገቢ ያደረገ ሲሆን ቀሪው ብር 2.3 ቢሊዮን ገንዘብ ሚኒስቴር ገቢ ባለማድረጉ የተከፋይ ሂሳቡ ላይ በእዳ የተቀመጠ መሆኑ፤

በኦዲቱ ታይቷል፡፡

በኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት እና የየብስ ወደቦች አገልግሎት አሰጣጥ

196. በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ከውጭ ሀገር በጅቡቲ ወደብ ወደ ሀገር ውስጥ ደረቅ ወደቦች፣ ቦንድድ መጋዘኖች እና ኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚጓጓዙ የኮንቴይነር ጭነቶችና ተሽከርካሪዎች የትራንዚት ሂደታቸውን ጠብቀው በተፈለገው የመዳረሻ ቦታዎች በወቅቱ እየደረሱ አለመሆኑ፣ የድርጅቱ ደንበኞች ለተደጋጋሚ እንግልትና ቅሬታ እየተዳረጉ መሆኑና ድርጅቱ የትራንዚት ሂደታቸውን ጠብቀው እንዲጓጓዙ ችግሩን ሊቀርፍ በሚያስችል መልኩ የዘረጋው የአሰራር ስርዓት አለመኖሩ እና ለተግባራዊነቱ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር አለማድረጉ፣

197. ድርጅቱ በመልቲ ሞዳል ትራንስፖረት አገልግሎት ከዉጭ ሀገር በጅቡቲ ወደብ ወደ ሃገር ዉስጥ መዳረሻ ቦታዎች ላጓጓዛቸው እንዲሁም ልዩ ድጋፍ ተጠቃሚ ለሆኑ ድርጅቶች፣ ለሰጠው አገልግሎት መሰብሰብ የሚገባውን በወቅቱ መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከትራንስፖርት አገልግሎት፣ ከኮንቴይነር ዲመሬጅ፣ ከመኪና ዲመሬጅ፣ ከአገልግሎት ክፍያ፣ ከወደብ ክሊራንስ እና ከየብስ ትራንስፖርት በድምሩ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ግዜ ድረስ ብር 2,394,413,088.97 መሰብሰብ የነበረበትን ያልተሰበሰበ ሲሆን፡፡ በተጨማሪም የአገልግሎት ክፍያው በዶላር መከፈል ካለባቸዉ የተለያዩ ድርጅቶች USD 5,404,103.99 ይህ ኦዲት እስከተጠናቀቀበት ግዜ ድረስ ያልተሰበሰበሰ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡ በተጨማሪም መመለስ ካለበቸው ኮንቴይነሮች ከተለያዩ ድርጅቶች 841 ኮንቴይነሮች ያልተመለሱ መሆኑ፣

198. በወደቡና በተርሚናሉ በሚገኙ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በመለዋወጫ እጥረት 28 እና በብልሽት 10 ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ማሽነሪዎች መገኘታቸው፣

199. በሞጆ ወደብና ተርሚናል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ከ800 በላይ ጉዳት ደርሶባቸው የሚገኙ ባዶ ኮንቴይነሮች መኖራቸውና፣ከ3,261 ቀናት ወይም ከ8 ዓመታት በላይ በወደቡ ውስጥ ሳይወገዱ ተከማችተው የሚገኙ ዕቃዎች እና በባዶ ኮንቴይነሮች ውስጥ ለ11 ዓመታት የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው የተለያዩ ቀሪ ዕቃዎች ተከማችተው መኖራቸው፣ ለረጅም ዓመታት በዝግ መጋዘኖችና በኮንቴይነሮች ውስጥ ተቆልፎባቸው ሳይወገዱና ውሳኔ ሳያገኙ ተቀምጠው የሚገኙ መኖራቸውና በመቆየታቸው ለብልሽት እየተዳረጉ መሆኑ በተጨማሪም በወደቡ ውስጥ መጨናነቅ በመፍጠር በኦፕሬሽን ስራው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እየፈጠሩ እና ድርጅቱን ለከፍተኛ ወጪ እየዳረጉት መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቀት ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>በፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት ለፐብሊክ ሰርቪስ ተጠቃሚዎች የሚሰጠው የትራንስፖርት አገልግሎት በተመለከተ፣</u>

200. አገልግሎቱ ለፌዴራል መንግስት እና ለአዲስ አበባ ከተማ ሲቪል ሠርቪስ ሠራተኞች አግልግሎት ለመስጠት ከገንዘብ ሚኒስቴር እና ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጋር ለ186,084 ሰራተኞች በቀን ለደርሶ መልስ ለማመላለስ ውል ቢገባም አገልግሎት እየተሰጠ ያለው ግን ለ46,707 ሰራተኞች ወይም 25% ብቻ መሆኑ ነገር ግን ገንዘቡን የሚቀበለው በሰጠው አገልግሎት ሳይሆን በውሉ መሰረት መሆኑ፣

201. አገልግሎቱ አገልግሎት ለመስጠት ውል የገባቸውን ሠራተኞች ለማመላለስ በቂ አውቶብስ የሌለው መሆኑ፣

202. የሰርቪስ አገልግሎት የሚሰጡ አውቶብሶች ጠዋት እና ማታ አገልግሎት ሲሰጡ በእያንዳንዱ ፌርማታ ላይ ተሳፋሪን በማሳፈርና በማውረድ አገልግሎት የማይሰጡ/ የማይቆሙባቸው ፌርማታዎች መኖራቸው፣

203. ከተለያዩ የመንግስት መ/ቤቶች ለአገልግሎቱ ተመላሽ የተደረጉ የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት መታወቂያዎች በአገልግሎቱ ከተያዘው ዳታ (Data base) ላይ ተቀናሽ የማይደረጉ መሆኑ፡

በኦዲቱ ታይቷል፡፡

<u>በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የሀይል ማስተላለፊያ መስመሮች እና ማከፋፈያ ጣቢያ ፕሮጀክት አፈፃፀም</u>

204. ድርጅቱ በግንባታ ላይ ባሉም ሆነ ወደ ኦፕሬሽን የሚገቡ የኃይል ማስተላለፊያ መስመሮችና ማከፋፈያ ጣቢያዎች ላይ የሚስተዋለውን ሰው ሰራሽ ጉዳቶችን ለመከላከል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ስለመስራቱ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ችግሮች ታይተዋል፡፡

205. ፕሮጀክቶች ገና በግንባታ ላይ እያሉ እና ግንባታቸው ከተጠናቀቀ በኋላ የሀይል ማስተላለፊያ ታወሮች አገልግሎት መስጠት ሳይጀምሩ ብረታቸው የሚሰረቅ መሆኑ፣

206. ድርጅቱ ተከታትሎ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ ላይ ከክልሉና ከማህበረሰቡ ጋር በጋራ የሚሰራው ስራ አጥጋቢ ውጤት ያላመጣ መሆኑ እና እነዚህን ሰው ሰራሽ ጉዳቶች ለመቀነስ ቅድመ መከላከል ስራ አለመሰራቱ፤

207. ድርጅቱ ከክልሎች፣ ከወረዳዎች፣ ከዞኖች እና ከጸጥታ አካላት ጋር ወጥነት ያለው ቅንጅታዊ አሰራር የሌለው መሆኑ፣ በፕሮጀክቱ ላይ ችግሮች ሲከሰቱ ብቻ ለጸጥታና ለክልል አካላት በደብዳቤ የሚያሳውቅ መሆኑ፤

208. እንደ ተቋም የኃይል ማስተላለፊያ መስመርና ማከፋፈያ ጣቢያዎች ላይ የደረሱ ሰው ሰራሽ ጉዳቶችን (ስርቆት) ተመዝግበው የማይያዙ እና የማይታወቁ መሆኑ፤ ይሁን እና በኦዲቱ ወቅት ከቀረቡ ማስረጃዎች ከ2012-2014 ዓ.ም በሶስት ፕሮጀክቶች ላይ ብቻ 17,131,658.82 USD እና በብር 179,698,447.3 በሰው ሰራሽ ጉዳቶች/ስርቆት መድረሱ፤

209. እንዲሁም በተለያዩ ሪጅኖች በብር 10,016,777.31 ስርቆት/ጉዳት መድረሱን ለማወቅ ተችሏል፡፡

210. በመጨረሻም ከላይ የተጠቀሱትን ዋና ዋና ግኝቶች እና በዚህ ሪፖርት ያልተጠቀሱትን በማጠቃለል ተቋማቱ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት የማሻሻያ እርምጃ እንዲወሰዱ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የተከበሩ አፈ ጉባዔ!

የተከበሩ ም/አፈ ጉባዔና

የተከበሩ የመንግስት ወጪ አስተዳደር ቋ/ጉ/ቋ/ኮ/ሰብሳቢ

የተከበራችሁ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት!

ክቡራትና ክቡራን!

<u>የመ/ቤታችን ዋና ዋና የድጋፍ ዘርፍ አፈጻጸምን በሚመለከት</u>

<u>የለውጥና የመልካም አስተዳደር ሥራዎችን በተመለከተ</u>

211. *መ/ቤታችን የውጤት ተኮር ሥርዓት ግንባታ ተከትሎ ለእያንዳንዱ ሠራተኛ ስራን ቆጥሮ በመስጠት ሥራዎቹ እስከ ሠራተኛ ድረስ እንዲወርዱ ተደርገዋል፡፡ በየሳምንቱና በየአሥራ አምስት ቀኑ እንዲሁም በየወሩ ሥራዎችን መገምገም ተችሏል፡፡*

212. *በመ/ቤቱ መዋቅር መሰረት በኦዲት ዘርፍ 126 ቡድኖችና በድጋፍ ዘርፍ 24 ቡድኖች በድምሩ 150 ቡድኖችን በማደራጀት ወደ ሥራ ተገብቷል፤ በዚሁም መሠረት በዓመት ሁለት ጊዜ የስራ አፈጻጸም ምዘናም ወቅቱን ጠብቆ በመሞላት ላይ ነው፡፡*

213. *ከሀምሌ/2014 እስከ መጋቢት/2015 በ9 ወራት ውስጥ የተለያዩ አገልግሎት ለማግኘት ወደ መ/ቤታችን የመጡ 917 ተገልጋዮች ሁሉም ተገልጋዮች በአግባቡ ከመ/ቤቱ የተለያዩ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በአለም አቀፍ የኦዲት ስታንዳርድ መሰረት ባለፈው ዓመት የተከናወነው የኦዲተሮች የስራ ክፍል ስብጥር ወይም የሪሻፍሊንግ ስራ ኦዲተሮች ከኦዲት ተቋማት ጋር የነበራቸውን መላመድ የቀነሰ ሲሆን አዳዲስ እውቀትና ልምድ እንዲያገኙ አግዟል፡፡*

214. *የስነምግባር ችግሮችን በመለየት ተገቢውን ማስተካከያ ለማድረግ በ25 ዩኒቨርሲቲዎች እና በ4 ፌዴራል መ/ቤቶች ላይ መረጃ በማሰባሰብ የዳሰሳ ስራ እና ከሥራ ሥምሪት በፊት የዳሰሳ ጥናቱ ባመላከታቸው ነጥቦች ላይ ለሁሉም ኦዲተሮች ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ተሰርቷል፡፡ ይህ ክትትል ከተጀመረ በኋላም መሻሻሎች ታይተዋል፡፡ ለአብነት ከኦዲት ተደራጊ መስርያ ቤቶች መደለያ አበል እንክፈላችሁ ጥያቄን አንቀበልም ያሉ ኦዲተሮች መኖራቸው እና ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ያቀረበላቸውን አበል እንክፈላችሁ ጥያቄ በመረጃ አስደግፈው ጉዳዩ እንዲታይ ለመ/ቤታቸው ያቀረቡ መሆኑ፡፡*

215. በሌላ በኩል በተደረገው ክትትል እና ቁጥጥር በበጀት ዓመቱ የዲስፕሊን ጉድለት በተገኘባቸው 10 ሰራተኞች ላይ በመ/ቤቱ የዲስፕሊን ኮሚቴ ክስ ተመስርቶባቸው ከቀላል እስከ ከባድ የዲሲፕሊን እምርጃ ተወስዷል፡፡ በሌላ በኩልም 5 ቅሬታዎች የቀረቡ ሲሆን፤ 5ቱ ቅሬታዎች በወቅቱ ምላሽ አግኝተዋል፤

<u>ሴክተር ዘለል ሥራዎችን በተመለከተ</u>

216. በፋይናንስ እና ህጋዊነት እንዲሁም በክዋኔ ኦዲቶች ለሴቶች፤ ወጣቶች፣ ለአካል ጉዳተኞችና ለአረጋውያን ወዘተ በህግ የተጠበቁ መብቶች ተጠቃሚነትና የአገልግሎት ተደራሽነት በተመለከተ ሁሉም የሥራ ክፍሎች የሥርዓተ ፆታ ጉዳይን የዕቅዳቸው አካል አድርገው እንዲያቅዱና በኦዲቱ ትኩረት ሰጥተዉ እንዲያዩት ተደርጓል፡፡

217. በየ 2 ወሩ በመደበኛነት የሚካሄደው የመ/ቤቱ ሴት ሠራተኞች የልምድ መለዋወጫ መድረክ ተጠናክሮ በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ ዝቅተኛ የገቢ መጠን ያላቸውን የመ/ቤቱ ሴት ሠራተኞችን ለማበረታታት የማህበሩ አባል በሆኑ ሴት ሠራተኞች 10% ቁጠባ በመቆጠብ የካፒታል መጠኑን ብር 294,572.85 ላይ ማድረስ ተችሏል፡፡

218. የሴት ሰራተኞችን አቅም ከማሳደግ አንፃር የነፃ የትምህርት ዕድል በማፈላለግ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን 12 (አንዷ የተመረቀች) የመ/ቤታችንን ሴት ሠራተኞች ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ እንዲሁም በዝቅተኛ የስራ እርከን ላይ ለሚገኙ ሠራተኞች ለበዓል የሚሆን ድጋፍ ተደርጓል፡፡

219. የሴቶችን ድርብ ኃላፊነት ግምት ውስጥ በማስገባት የመስክ የሥራ ድልድል ሲደረግም ለሴት ኦዲተሮች ቅድሚያ በመስጠት ምቹ የሆነ የመስክ የሥራ ምደባ እንዲያገኙ በመደረጉ ውጤታማ እንዲሆኑ እገዛ ማድረግ ተችሏል፡፡

220. ለሰራተኞች የስራ አካባቢን ምቹ ከማድረግ አንፃር በመ/ቤቱ ክበብ በተመጣጣኝ ዋጋ የምግብ አገልግሎት እንዲሁም መሰረታዊ የፍጆታ ዕቃዎች በሴቶች ፎረም በኩል እየቀረበ ይገኛል፡፡

<u>የአቅም ግንባታ እና ከኦዲት ባለድርሻ አካላት ጋር የተሰሩ ስራዎችን በተመለከተ</u>

221. የመ/ቤታችን የሥልጠና ክፍሎች በእድሳት ምክንያት አገልግሎት መስጠት ባለመቻላቸው ሌሎች ከመ/ቤቱ ውጪ ያሉ ማሰልጠኛዎችን በመጠቀም ሥልጠና እየተሰጠ ይገኛል፡፡

222. በመ/ቤታችን 36 ዓይነት የሥልጠና ፍላጎቶችን በመለየትና በማኔጅመንት በማጽደቅ በመ/ቤታችን የስልጠና ባለሙያዎች፣ ከኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት፣ ከAFROSAI-e፣ ከአሜሪካ ዋና ኦዲተር መ/ቤት (GAO) እና ሌሎችም አካላት በመጠቀም በፀደቀው ካላንደር መሰረት ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡

223. በዚህም መሰረት በተለያዩ የስልጠና ርዕሶች ላይ በገጽ ለገጽ ለ458 ሴቶች እና ለ819 ወንዶች በድምሩ ለ1277 ሰራተኞች የአቅም ማጎልበቻ ሥልጠናዎች ተሰጥቷል፡፡ ከዚህ ውስጥ ለ5 ሴት እና ለ23 ወንድ በድምሩ ለ28 ሰራተኞች በተለያዩ የስልጠና ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የተሰጠው ስልጠና በቨርቹዋል (Zoom) የተወሰደ ነው፡፡

224. በተለይም በዚህ በጀት ዓመት የአመራሩን እና ሠራተኛውን የመፈጸም አቅም ከፍ ለማድረግ ከተቋሙ የበላይ ኃላፊዎች እስከ ከፍተኛ ኦዲተሮች ድረስ በአስተሳሰብ ግንባታ /Mindset/፣ በአመራር ክህሎት /Leadership/፣ በስሜት ብልህነት /Emotional Intelligence/ ተከታታይ የሆነ ስልጠና ለ176 ሠራተኞች እና የሥራ ኃላፊዎች ተሰጥቷል፡፡

225. በሌላ በኩል ለ60 የመ/ቤቱ ሠራተኞች እና 11 የክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሠራተኞች የትምህርት ዕድሎች የተሠጠ ሲሆን በዚሁም መሠረት ሁለተኛ ዲግሪ አገር ውስጥ 1፣ ውጭ ሀገር 1፣ ኤሲሲኤ (ACCA) ትምህርት ዋና ኦዲተር መ/ቤት 28 እንዲሁም ለክልል ዋና ኦዲተር 11 ሠራተኞች እየተማሩ የሚገኙ ሲሆን በተጨማሪም ዓለማቀፉ የዋና ኦዲተሮች ማህበር ዲቨሎፕመንት ኢኒሼቲቭ (IDI PESA-P) በሚሰጠው የሙያ ስልጠና እድል 19 ኦዲተሮች የተገኘውን የትምህርት እድል በኦን ላይን (online) ለአንድ ዓመት እየተከታተሉ ይገኛሉ፡፡ እንዲሁም በሀገር ውስጥ ለ10 ሠራተኞች የ2ኛ ዲግሪ ትምህርት ዕድል ተሰጥቶ በፈተና ሂደት ደረጃ ላይ ናቸው፡፡

226. በኦዲት ግኝቶችና መንስኤ ላይ ለፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች በተደጋጋሚ ለሚገኙ ግኝቶች መንስኤ እና የውስጥ ኦዲተሮች ሚና ላይ ገንዘብ ሚኒስቴር ባዘጋጀው ሥልጠና መድረክ ላይ ከ 170 የፌደራል ተቋማት እና 11 ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት እና 2 ከተማ አስተዳደሮች የተገኙ 196 የኢንስፔክሽን ሰራተኞች አሰልጣኝ በመመደብ የአቅም ግንባታ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

227. በሌላ በኩል ለሌሎች አካላት አቅም ግንባታ ድጋፍ ከማድረግ አንጻር ለ12 ክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች፣ ለ6 ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች እንዲሁም ለመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት በድምሩ ለ1,247 ሠራተኞች እና የሥራ ኃላፊዎች የተለያዩ የአቅም ግንባታ ሥልጠና እና የግንዛቤ ማስጨበጫዎች ተሰጥቷል፡፡

<u>የኦዲት ባለድርሻ አካላት የጋራ መድረክ እና መረጃዎችን ተደራሽ ማድረግን በተመለከተ</u>

228. የ21ኛው የዋና ኦዲተሮች የምክክር ጉባኤ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ቋሚ ኮሚቴ አመራሮች፣ የየክልሎች ምክር ቤቶች የዋና ኦዲተሮችን ስራ ክትትል የሚያደርጉ ቋሚ ኮሚቴ አመራሮች፣ የገንዘብ ሚኒስቴር የስራ ኃላፊዎች፣ የሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች አፈ-ጉባኤዎች፣ ዋና ኦዲተሮች፣ የፋይናንስ ቢሮ ሃላፊዎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በተገኙበት በሀረር ከተማ ተካሂዷል፡፡ በዚህ ጉባኤ በ20ኛው የዋና ኦዲተሮች ጉባኤ ውሳኔዎች አፈፃፀም ላይ የሁሉም ባለድርሻ አካላት ሪፖርት ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል፣ እስከ ቀጣይ ጉባኤ የሚፈፀሙ ውሳኔዎችን አሳልፏል፡፡ በጉባኤው የውጭ ኦዲት ድግግሞሽን ለማስቀረት የነጠላ ኦዲት አዋጅ ቁጥር 1251/2013 የአፈፃፀም መመሪያ ላይ ውይይት በማድረግ በአራት ክልሎች በፓይለት ደረጃ ኦዲቱ እንዲጀመር ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡

229. የመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ባካሄዳቸው 26 ይፋዊ ህዝባዊ ስብሰባዎች እና 8 የመስክ ጉብኝቶች በድምሩ 34 መድረኮች ላይ በመገኘት በተነሱ ጉዳዮች ላይ ተገቢ ማስረጃ በመስጠት ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም የይፋዊ ስብሰባዎች፣ በመ/ቤቱ የተሰጡ የግንዘቤ ማስጨበጫዎች፣ የተለያዩ ሁነቶች፣ የሚዲያ ዳሰሳ ውጤቶችን፣መጣጥፎችን በመጠቀም እና ዜናዎችን በማዘጋጀትና በማሰራጨት መ/ቤቱን በተለያዩ ሚዲያዎች የማስተዋወቅ ስራ ተሰርቷል፡፡

230. ኦዲት ያስገኛቸው ፋይዳ በሚል ርዕስ መ/ቤታችን ለ20 አመታት ያከናወናቸው ኦዲቶች በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለማስጠናት ስምምነት ላይ ተደርሷል፤ በዩኒቨርሲቲው ለጥናቱ የሚሆን የመረጃ ማሰባሰብ ሥራ ተጀምሯል፡፡

231. ከፕሬስ ድርጅት ጋር በመተባበር "ለፀረ-ሙስና ትግሉ ምርመራ ጋዜጠኛነት" በሚል መሪ ቃል ለሚዲያ አመራሮች፣ ጋዜጠኞችና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያዎች በምርመራ ጋዜጠኝነት ላይ በአዳማ ከተማ ለ2 ቀን በተዘጋጀው ስልጠና ላይ ለ150 ተሳታፊዎች ስለ መ/ቤታችን ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ ተሰርቷል፡፡

232. በሁለት የተለያዩ መድረኮች በአጠቃላይ 63 ለሚሆኑ ለቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዎች እና ምክትል ሰብሳብዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

233. የአረንጓዴ አሻራን ታሳቢ በማድረግ አካባቢንና ማህበራዊ ሁኔታን የሚመለከቱ ስራዎችን ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ሠራተኞች፣ ከመንግሥት ወጪ አስተዳደር ቋሚ ኮሚቴ እና ከክልል ዋና ኦዲተሮች እና ከሌሎችም ባለድርሻ አካላት በጋራ በመሆን የአረንጓዴ አሻራ የችግኝ ተከላ ተከናውኗል፡፡

234. በ2015 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች የባለድርሻ አካላት የ6 ወራት ዕቅድ አፈጻጸም ላይ ተቀባይነት የሚያሳጣ የኦዲት አስተያየት የተሰጠባቸው የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች የኦዲት ግኝት ማስተካከያ የድርጊት መርሃ ግብር እንዲያቀርቡ ከሚጠበቅባቸው 44 መ/ቤቶች መካከል 34 መ/ቤቶች የድርጊት መርሃ ግብር ያቀረቡ ሲሆን፣ 10 መ/ቤቶች ያላቀረቡ መሆናቸውን በክትትል ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>የመ/ቤቱ የሰው ሀብት ሁኔታ</u>

235. ለመ/ቤቱ በመዋቅር የተፈቀደው የሰው ኃይል የኦዲት ባለሙያ 669፣ የድጋፍ ሰጪ ሠራተኛ 344 በድምሩ 1013 የሰው ኃይል በ5 ዓመቱ የስትራቴጂክ እቅድ ዘመን የሚሟላ ተፈቅዷል፡፡ የኦዲት ሥራው በየካቲት ወር 2014 ሲጀመር 441 ኦዲተሮችና 188 የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በድምሩ 629 ሠራተኞች በሥራ ላይ ነበሩ፡፡ በኦዲት ዓመቱ ውስጥ 73 ኦዲተሮችና 28 ሰራተኞች ለድጋፍ ዘርፍ በድምሩ 101 ሠራተኞች ተቀጥረዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ከስራ የለቀቁት በገዛ ፈቃዳቸው ከኦዲት 40 ከድጋፍ 16 በድምሩ 56 ሰራተኞች፣ በጡረታ 7፣ በሞት 1 በአጠቃላይ 64 ሰራተኞች በተለያየ ምክንያት መ/ቤቱን ለቀዋል፡፡

236. በመሆኑም በኦዲት ዓመቱ መጨረሻ በመ/ቤቱ 473 የኦዲት ባለሙያዎች (310 ወንድ እና 163 ሴት)፣ 192 የድጋፍ ሰጪ (87 ወንዶችና 105 ሴቶች) ሠራተኞች 2 የበላይ ኃላፊዎች በአጠቃላይ 667 ሠራተኞችና ኃላፊዎች በሥራ ላይ ነበሩ፡፡ ክፍት የሥራ መደቦችን ለማሟላት ከፍተኛ ጥረት የሚደረግ ይሆናል፡፡

የ2014 በጀት ዓመት የበጀት አጠቃቀም

237. ለ2014 በጀት ዓመት በመ/ቤታችን ሊከናወኑ ለታቀዱት ሥራዎች ማከናወኛ መደበኛ በጀት ብር 115,905,746.00 የተፈቀደ ሲሆን ለዓመቱ ከተፈቀደው በጀት ውስጥ ብር 107,236,462.65 (92.52%) መጠቀም ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሰየማቸው ገለልተኛ ኦዲተሮች ኦዲት ተደርጎ ከስህተት የጸዳ (clean) አስተያየት የተሰጠው ሲሆን ሪፖርቱም ለም/ቤቱ ተልኳል፡፡

2015 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወር የበጀት አጠቃቀም

238. ለ2015 በጀት ዓመት በመ/ቤታችን ሊከናወኑ ለታቀዱት ሥራዎች ማከናወኛ መደበኛ የተስተካከለ በጀት ብር 160,523,312.38 እና ለህንፃ ዕድሳት ብር 100,000,000.00 በድምር ብር 260,523,312.18 የተፈቀደ ሲሆን ለዓመቱ ከተፈቀደው በጀት ውስጥ በዘጠኝ ወራት ጊዜ ውስጥ ለመጠቀም የታቀደ ብር 119,095,219.52 ሲሆን በዕቅዱ መሠረት ብር 111,347,353.37 (93.49%) መጠቀም ተችሏል፡፡ የህንጻው ግንባታ ቅድመ ክፍያ ብር 80,929,765.93 ተፈጽሞ በግንባታ ሂደት ላይ ይገኛል፡፡ የተቀረው በጀት ብር 49,175,959.01 በቀሪ ወራት ውስጥ ለማከናወን ለታቀዱት ተግባራት በዕቅዱ መሠረት ሥራ ሊይ የሚውል ይሆናል፡፡

ቴክኖሎጂ አጠቃቀም በተመለከተ

239. የመ/ቤቱ ሥራዎች በቴክኖሎጂ በማስደገፍ የኦዲት አሠራር የሚያዘምኑና የመ/ቤቱን የመረጃ ስርዓቶች ተመጋጋቢ እንዲሆኑ የሚያደርጉ የመ/ቤቱን ሥራ ከማቀላጠፍ፣ ወረቀት አልባ ተቋም ለማድረግና ባለፉት አመታት ስራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡ የኦዲቱን ስራ በሲስተም በማገዝ ምቹ እና ቀላል ለማድረግ ስራዎቻችንን በቴክኖሎጂ የማዘመን ስራ ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡

መ/ቤቱን ያጋጠሙ ችግሮና የተወሰዱ እርምጃዎች

240 በአፈጻጸም ወቅት መ/ቤቱን ካጋጠሙት ችግሮች መካከል ዋና ዋናዎቹ የተቀናጀ የፋይናንስ አስተዳደር የመረጃ ሥርዓት (IFMIS) መቆራረጥ፣ እና በፀጥታ ችግር ምክንያት የኦዲት ሥራዎችን በታቀደው ዕቅድ መሠረት ማጠናቀቅ አለመቻል፣ ዩኒቨርሲቲዎች ለ12ኛ ክፍል ፈተና ለአንድ ወር ጊዜ በመዘጋታቸው በኦዲቱ ሥራ ላይ ተጽዕኖ ማሳደሩ፣ የተዋሃዱ እና የፈረሱ መ/ቤቶች ትክክለኛ የሂሳብ ሚዛን ለይቶ ለማቅረብ ጊዜ ከመውሰዱም በተጨማሪ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች በመቀያየር ምክንያት በወቅቱ ለኦዲት መረጃን ማግኘት አለመቻል፣

241 የመ/ቤት ኃላፊዎች በመውጫ ስብሰባ ወቅት አለመገኘትና የኦዲት ጊዜውን ማንተት እንዲሁም ከመውጫ ስብሰባ በኋላ በርካታ ዶክመንቶች አሉን በማለት ለማጣራት ተጨማሪ ጊዜ በመውሰዱ ኦዲቱ በወቅቱ እንዳይጠናቀቅ ችግር መሆን፣

242 ለኦዲት ተደራጊዎች ለተላከው ፋክት ሽት እና ለረቂቅ ሪፖርት በወቅቱ ምላሽ አለማግኘት፣

243 የሂሳብ ሪፖርቶችን በወቅቱ ዘግቶ አለማቅረብ፣ የሥራ ቢሮና የሂሳብ ዶክሜንቶች በተቀመጠ ጊዜ ገደብ ውስጥ ተዘጋጅቶ ለኦዲት ሥራ አለማድረስ፣

244 ለኦዲተሮች በመስክ ስራ ላይ በሚቆዩበት ጊዜ የሚከፈለው ውሎ አበል አነስተኛ በመሆኑ ከኑሮ ውድነቱ አንጻር በቂ ባለመሆኑ ጫና መፍጠሩ፣ የሚሉት ናቸው፡፡

245 ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች ለመፍታት የፀጥታ ችግር ባለባቸው ቦታዎች አንፃራዊ ሰላም ወደአለባቸው ቦታዎች ሠነድ አንጉዞ በመስራት፣ የዩኒቨርሲቲዎችን ኦዲት ደግሞ ተጨማሪ የሰው ኃይል በመመደብ እንዲሁም ረቂቅ ሪፖርት ከመላኩ በፊት አስቀድሞ የመውጫ ስብሰባ በማድረግ ጊዜውን በአግባቡ በመጠቀም እና ሌሎችን ችግሮች ደግሞ ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ጋር በመነጋገር ችግሮችን መፍታት ተችሏል፡፡ ያልተፈቱ ችግሮች ቢኖሩም ችግሮቹን በመቋቋም ስራዎቻችንን በአቀድነው መሰረት ጥሩ በሚባል አፈፃፀም ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡ ከመስክ አበል ጋር የተያያዘውን ችግር በተመለከተ ችግሩን ለመፍታት ከኦዲት ኮሚሽን ጋር በጋራ በመሥራት ላይ እንገኛለን፡፡

የ2015/16 ኦዲት ዓመት ዕቅድ

246 የመ/ቤቱ የ5 የእስትራቴጂክ ዕቅድ ክለሳ (Strategic Plan Review) በማድረግ ሁሉም የመ/ቤቱ ሰራተኞችን በማሳተፍ ተገምግሞና አስተያየት ተሰጥቶበት ወደ ትግበራ ተገብቷል፡፡ በዚህም መሠረት በ2015 በጀት ዓመት በጀት ከተመደበላቸው 179 የፌዴራል መ/ቤቶች እንዲሁም 57 ቅርንጫፎች ውስጥ 11 መ/ቤቶች ሂሳባቸው በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ኦዲት እንደሚደረጉ ታሳቢ ተደርጎ የተቀሩትን 168 መ/ቤቶች 57 ቅርንጫፎች በመ/ቤታችን ኦዲት በማድረግ የፋይናንስና የሕጋዊነት ኦዲት ሽፋኑን 100% ለማድረስ ታቅዷል፡፡ እንደዚሁም ከመጋቢት 2015 እስከ ጥር 2016 ድረስ ባለው ጊዜ 32 አዳዲስ የክዋኔ ኦዲቶችን እና 12 ክትትል ኦዲቶችን በማከናወን 44 የክዋኔ ኦዲት ሪፖርቶችን ለማውጣት ከባለፈው አመት በ14 ኦዲቶች ሽፋኑን በማሳደግ እና አንድ የኢንፎርሜሽን ሲስተም ኦዲት ለማከናወን ታቅዷል፡፡ በተጨማሪም የመሠረታዊ አገልግሎት ተጠቃሚ በሆኑ ወረዳዎችና የሴክተር ቢሮዎች 313 የተከታታይ ኦዲት በየሩብ ዓመቱ ለማከናወን እና 23 የማረጋገጥ ስራዎች (Verifications); እንደዚሁም አንድ ፕሮግራም አቀፍ ኦዲት በገንዘብ ሚኒስቴር ደረጃ ለማካሄድ በእቅድ ተይዟል፡፡

በሂሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወነ ኦዲት

247 የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በማቋቋሚያ አዋጁ በተሰጠው ኃላፊነት ራሱ ከሚሰራው በተጨማሪ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን፣ ፕሮጀክቶችንና የእርዳታ ሂሳቦችን በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተሰጣቸው የግል ኦዲት ድርጅቶች ኦዲት በማስደረግ ላይ ይገኛል፡፡ በዚሁ መሠረት በኦዲት ድርጅቶቹ ኦዲት ተደርገው በሚቀርቡ ሪፖርቶች መነሻነት አስፈላጊው የማሻሻያ እርምጃዎችን እንዲወሰዱ ለኦዲት ተደራጊ ድርጅቶች እና ለተቆጣጣሪ መ/ቤቶች አስፈላጊው ማሳሰቢያ ተሰጥቷል፡፡

248 በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እና በግል የኦዲት ድርጅቶች በ2014 በተከናወኑና ለመ/ቤታችን የደረሱ ኦዲቶች ላይ የታዩ ጎላ ጎላ ያሉ ግኝቶች በዋና ኦዲተር መ/ቤት ዘገባ ጥራዝ 2 ክፍል 3 በዝርዝር የቀረበ ስለሆነ ዝርዝሩን ከዚያው መመልከት ይቻላል፡፡

የመንግስት ልማት ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች ኦዲት ክትትል

249 በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽንና በግል ኦዲት ድርጅቶች የተከናወኑ ከግንቦት 1/2014 እስከ ሚያዚያ 30/2015 ዓ.ም ሪፖርታቸው ለመ/ቤታችን የቀረቡ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችና በሽርክና የተቋቋሙ ድርጅቶች 27 (የተለያዩ ዓመታት በጀት ዓመት ሪፖርትን በመቁጠር) ሲሆኑ፣ በኢትዮጵያ መንግሥትና በልማት አጋር ድርጅቶች የጋራ ትብብር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ሂሳብ ኦዲት 116 በድምሩ 143 (ይህ ቁጥር በበጀት ዓመቱ የሁለት እና ከዚያ በላይ በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረገ ድርጅት ወይም ፕሮጀክት እያንዳንዱን ሪፖርት በመቁጠር የተወሰዱ) ናቸው፡፡

250 ለመ/ቤታችን ከደረሱን የመንግስት የልማት ድርጅቶች የኦዲት ሪፖርቶች በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሠረት ሲተነተን አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ የሌለበት (Unqualified Opinion) አስተያየት የተሰጠባቸው 12፣ ከጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ቢሆንም ነቀፌታ ያለበት (Qualified Opinion) አስተያየት የተሰጠባቸው 8፣ አቋም ለመውሰድ የማይቻል በመሆኑ አስተያየት ያልተሰጠባቸው (Disclaimer Opinion) 7፣ ሲሆን የፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች ኦዲቶች በኦዲት አስተያየት ሲተነትን አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ የሌለበት (Unqualified Opinion) አስተያየት የተሰጠባቸው 82፣ ከጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ቢሆንም ነቀፌታ ያለበት (Qualified Opinion) አስተያየት የተሰጠባቸው 28፣ አቋም ለመውሰድ የማይቻል በመሆኑ አስተያየት ያልተሰጠባቸው (Disclaimer Opinion) 6 ናቸው፡፡

የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን የፋይናንስ እንቅስቃሴ

251 የኮርፖሬሽኑ የገቢ ምንጭ በዋናነት የተመሰረተው ለተለያዩ የመንግስት የልማት ድርጅቶችና ሌሎች መንግስታዊ ተቋማት (ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች) ከሚሰጠው የኦዲት አገልግሎት ከሚያስከፍለው የአገልግሎት ዋጋ በተጨማሪ ከልዩ አገልግሎቶች ማለትም ከማማከርና ከልዩ ኦዲት ሥራ እንዲሁም ከሕንፃው ቢሮዎች ከሚገኝ የኪራይ ገቢ ነው፡፡

252 ኮርፖሬሽኑ በ2014 በጀት ዓመት ከኦዲት ሥራና ከማማከር አገልግሎት እንዲሁም ከቤት ኪራይ ብር 56,253,735 ገቢ ለማግኘት አቅዶ ብር 73,997,243 ገቢ ያገኘ ሲሆን፣ በበጀት ዓመቱ ብር 40,249,650 ወጪ ለማድረግ አቅዶ ብር 40,197,499 ወጪ ያደረገ ሲሆን፣ በበጀት ዓመቱ ብር 23,659,820 የተጣራ ትርፍ ሊያገኝ ችሏል፡፡

ማጠቃለያ

253 የ2014 በጀት አመት ሂሳብ ላይ የተካሄደው የፋይናንስ እና ህጋዊነት ኦዲት በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን እንደሚሰሩ የታቀዱትን ጨምሮ በወቅታዊ ሁኔታ ከተቋረጠው አንድ መ/ቤት እና ሶስት ቅርንጫፎች በስተቀር በተቀሩት የፌደራል ባለበጀት መ/ቤቶች ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡ አፈጻጸሙም (99.4%) ሆኗል፡፡

254 በሌላ በኩልም የክዋኔ ኦዲትን እቅድ አፈጻጸም በተመለከተ 23 አዲስ፣ ከአምናው የዞረ 1 ኦዲት እና 7 የክትትል ኦዲት በድምሩ 31 ለመስራት ታቅዶ የ23 አዳዲስ ከባለፈው አመት የዞረው አንደ ኦዲት ተጨምሮ 24 እና 8 የክትትል ኦዲት በድምሩ የ32 የክዋኔ ኦዲት ሪፖርቶች ወጪ ተደርገዋል፤ አፈጻጸሙ 103.22% ሆኗል፡፡

255 የ2014 በጀት አመት የኦዲት ውጤት ሲታይ ነቀፌታ የሌለበት 73፣ ከጥቂት ጉድለቶች በስተቀር አጥጋቢ ሆነው የተገኙ 66፣ አስተያየት መስጠት ያልተቻለባቸው 6 እና የጎላ ችግር ያለባቸው ሆኖ በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጣቸው 19 ናቸው፡፡

256 የግኝቶቹም ባህሪ ሲታይ የጥሬ ገንዘብ እና የባንክ ሂሳብ አያያዝ፣ ውዝፍ ሂሳቦች በወቅቱ አለመሰብሰብ እና አለማወራረድ፣ ተከፋይ ሂሳቦች፣ በብልጫ (አለአግባብ) የተከፈሉ ክፍያዎች፣ በገቢ ግብር ቀረጥና ታክስ አዋጅ ደንብ እና መመሪያ መሰረት አለመሰብሰብ ፣ደንብ እና መመሪያዎች ያልጠበቁ ግዢዎች፣ የዉስጥ ገቢ አሰባሰብ እና አጠቃቀም፣ የበጀት አስተዳደር እና የመንግስት ንብረት አጠቃቀም እና አስተዳደር የሚታዩ ጉድለቶች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በሌላ በኩልም በበጀት አመቱ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በተደረጉ ክዋኔ ኦዲቶች በርካታ የአሰራር ስርዓቶች በየመ/ቤቶቹ ተዘርግተው የማይትገበሩ መኖራቸው ዋና ዋና ግድፈቶች ሆነው ተገኝዋል፡፡

257 በዚሁ መሰረትም የፋይናንስና ህጋዊነት ሆነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርቶች ጉድለቶችን ከማሳየት ባሻገር የታዩ የአሰራር ጉድለቶች እና ክፍተቶችን ለማረም እና ለማስተካከል የሚያስቸሉ የመፍተሄ ሃሳቦችን ጭምር ያካተቱ ከመሆኑም በላይ አብዛኛዎቹ የተሰጡት ማሻሻያ ሃሳቦች በኦዲት ተደራጊዎችም ጭምር ስምምነት የተደረሰባቸው ናቸው፡፡

258 ስለዚህ ዝርዝር የፋይናንስ እና ህጋዊነት ኦዲት ሪፖርቱ አጠቃላይ ዘገባ በሁለት ጥራዝ እንዲሁም የእያንዳንዱ ክዋኔ ኦዲት ዝርዝር ሪፖርቶች አስተያየት ሊሰጥባቸዉ ያልተቻለ የፋይናንስ እና ህጋዊነት ኦዲት ሪፖርቶች እና ተቀባይነት የሚያሳጣ አሰተያየት የተሰጣቸዉ መ/ቤቶች ኦዲት ሪፖርቶች አንድ ላይ ተደራጅተዉ በሲዲ ለተከበሩ አፈጉባዔ የተላኩ በመሆኑ ሪፖርቶቹን የም/ቤቱ የመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎችም ጉዳዩ የሚመለከታችሁ ቋሚ ኮሚቴዎች ጭምር በጥልቀት ታይተው እና ተመርምረው ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ክትትል እና ግፊት ሊደረግ ይገባል፡፡

259 የተጠያቂነት ስርዓትን ከማረጋገጥ አንጻር ፡የመንግሰት ወጪ አሰተዳደር ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የጀመረውን ግልጽ ይፋዊ መድረክ አጠናክሮ እዲቀጥልበት በአክብሮት እየጠየኩ ከዚህ በተጨማሪም የገንዘብ ሚኒስቴር እና የፍትሕ ሚኒስቴር በግልጽ ይፋዊ መድረኮች ባደረጉት ተሳትፎ እንዲሁም በዓመቱ የወሰዷቸውን አስተዳደራዊ እርምጃዎች ተሳትፎዎች አጠናክረው እንዲቀጥሉበት እየጠየኩ፣ የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን፣ የፕላን እና ልማት ሚ/ር እና የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን ባደረጉት የህዝባዊ ስብሰባዎች ተሳትፎ በራሴና በመ/ቤቴ ስም እንዳመሰግን

ይፈቀድልኝ፡፡ በመጨረሻም መላው ሰራተኞቻችን እቅዳችን እንዲሳካ ላበረከቱት አስተዋጽኦ በምክር ቤቱ ፊት እንዳመሰግን ይፈቀድልኝ፡፡

በጥሞና ስላዳመጣችሁኝ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

አባሪ 1

በ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት እና ባለፉት ተከታታይ ሁለት ኦዲቶች

	ሀ	ሂሣባቸው የጎላ ችግር ያለበት በመሆኑ ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጣቸው /Adverse opinion/			X
	ለ	አስተያየት ለመስጠት ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች /Disclaimer Opinion/			XX
	ሐ	ከጥቂት ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ ሒሳባቸው አጥጋቢ በመሆኑ ነቀፌታ ያለበት (Except for) የተሰጣቸው			E
	መ	ነቀፌታ የሌለበት የኦዲት አስተያየት የተሰጣቸው(Clean opinion)			C
ተ.ቁ		የመ/ቤት ስም	ኦዲት የተደረገው በጀት ዓመት		
			2012	2013	2014
		ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት			
1	1	የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ	X	X	X
2	2	የጂንካ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
3	3	የደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ	E	E	X
4	4	የጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ		X	X
5	5	የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
6	6	የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ	X	E	X
		የፋይናንስና ኮሚዩኒኬሽን መ/ቤቶች			
7	1	የሪፐብሊኩ ጥበቃ ኃይል	XX	XX	XX
8	2	የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት			XX
9	3	የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት		XX	XX
10	4	የቀድሞው ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት			XX
11	5	የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አገልግሎት			X
12	6	የፌዴራል ስነምግባርና ፀረሙስና ኮሚሽን			X
13	7	የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት	X	X	X
14	8	የኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ			X
15	9	የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን	X	X	X

16	10	የዱር እንሰሳት ጥበቃ ባለሥልጣን			X
17	12	ቱሪዝም ሚኒቴር	XX	X	X
		የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች			
18	1	አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ	X	E	X
19	2	ቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ	X	X	X
20	3	የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር	XX	XX	X
21		የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር			X
22	4	የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን	XX	XX	XX
		ንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች			
23	1	የኢትዮጵያ ማሪታይም ባለስልጣን		C	X
24	2	የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር			XX
		የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች			
25	1	የታላቁ ህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽ/ቤት	X		X

አባሪ 2

የልዩ ኦዲት ሥራዎች፣

1. ዲላ ዩኒቨርሲቲ
2. ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ
3. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የዛግዌ ህንፃ ግንባታ ፕሮጀክት ኦዲት
4. የኤ.ቢ.ኤች ኮንሰልታንሲ ኃ/የተ/የግ/ ማህበር እና ጅማ ዩኒቨርሲቲ የጋራ ትምህርት ፕሮግራም የገቢና የወጪ ሂሳብ
5. ትራንስፖርትና ሎጂስቲክ ሚኒስቴር
6. ብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን የአሁኑ ኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ--የኦሞ ኩራዝ 1፣ የወልቃይት፣ የከሰም፣ የጣና በለስ 1፣ የጣና በለስ 2፣ የጣና በለስ 3 ስኳር ፋብሪካዎች ፕሮጀክት እንዲሁም የወልቃይት 3ሺ ሄክታር እና የጣና በለስ 10ሺ ሄክታር የድራግ ሆዝ የመስኖ ርጭት ዘዴ (Sprinkler Irriጵation System)

7. ኢትዮጵያ ስኳር ኮርፖሬሽን የአሁኑ የኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ፡- የነባር ስኳር ፋብሪካዎች የማስፋፊያ ፕሮጀክቶች እና አዳዲስ አስር/10/ የፋብሪካዎች ግንባታ እና ተያያዥ ስራዎች

8. ኢትዮጵያ ስኳር ኮርፖሬሽን የአሁኑ የኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ፡- የመተሐራ ስኳር ፋብሪካ በተመለከተ

9. ኢትዮጵያ ስኳር ኮርፖሬሽን የአሁኑ የኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ፡- የፍንጫአ ስኳር ፋብሪካ

10. የመደ ወላቡ ዩኒቨርስቲ

11. የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ሆለታ ግብርና ምርምር ማዕከል ናቸው፡፡

<u>የልዩ ኦዲት ሥራዎች እየተከነወኑ የሚገኙ</u>

1. የኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኮርፖሬሽን
2. አርዳይታ ግብርና ኮሌጅ
3. የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን
4. የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ
5. የኢትዮጵያ ፓራሎምፒክ ኮሚቴ
6. የኢትዮጵያ ፐልፕና ወረቀት አ.ማህበር
7. የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
8. ድል በትግል የገቢያ ማዕከል አክስዮን ማህበር
9. የሰላሌ ዩኒቨርሲቲ የ2011 በጀት ዓመት የተለያዩ ግዢዎች በሥራ ላይ ይገኛሉ፡፡

አባሪ 3

	ሂሳባቸውን በወቅቱ ያልዘጉ መ/ቤቶች	የሒሳብ ሪፖርቱ የቀረበበት ቀን

	ሂሳባቸውን በወቅቱ ያልዘጉ መ/ቤቶች	የሒሳብ ሪፖርቱ የቀረበበት ቀን
	የመ/ቤቱ ስም	
	ፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	
1	ቱሪዝም ሚኒስቴር	8/3/2015
2	የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም	23/2/2015
3	የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት	1/3/2015
4	የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልገሎት	22/2/2015
5	የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት	41675
6	የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን	18/2/2014
7	የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት	15/03/2015
8	የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት	42038
9	የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን	30/02/2015
10	የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት	11/4/2015
11	የፕላንና ልማት ሚኒስቴር	42279
12	የመንግስት ኮመኒኬሽን አገልግሎት	11/4/2015
	ልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	
1	የግብርና ሚኒስቴር	12/4/2015
2	የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር	26/03/2015
3	የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት	10/6/2015
4	የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታልና ሚሊኒየም የህክምና ኮሌጅ	23/02/2015
5	የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር	7/4/2015
6	የጤና ሚኒስቴር	24/04/2015
	ንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	
1	የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር	8/7/2015
2	የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን	16/2/2015
3	ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር	1/3/2015
4	የኢትዮጲያ ብሄራዊ ትያትር	7/3/2015
5	የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽ/ቤት	21/4/2015
6	የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት	22/3/2015
7	የጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት	2/6/2015
8	የኢትዮጲያ ኢንተርፕራይዝ ልማት	16/5/2015
9	ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር	15/2/2015
10	የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት	22/3/2015
11	ህገመንግስትና ፌደራሊዝም አስተምዕሮ ማዕከል	22/3/2015
12	ነዳጅና ኢነርጂ ባለስልጣን	17/05/2015
13	ፍትህ ሚኒስቴር	8/3/2015
14	የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	28/04/2015

	ሂሳባቸውን በወቅቱ ያልዘጉ መ/ቤቶች	የሒሳብ ሪፖርቱ የቀረበበት ቀን
15	የቀድሞው ኢትዮጲያ ደረጃዎች ኤጀንሲ	10/4/2015
16	የህገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ጽ/ቤት	2/6/2015
17	የፕሬዝደንት ጽ/ቤት	23/05/2015
18	የቀድሞው መድን ፈንድ አገልግሎት	4/5/2015
19	የፌደራል ፍትህና ህግ ኢንስቲትዩት	9/2/2015
20	የኢትዮጵያ ፀረ አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን	29/3/15
	አቅም ግንባታ መ/ቤቶች	
1	የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር	9/3/2015
2	የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር	30/03/2015
3	የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት	30/03/2015
4	የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር	30/03/2015
5	የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን	20/03/2015